እስራኤል ሕፃን በነበረ ጊዜ ወደድኩት፤
ልጄንም ከግብፅ ጠራሁት፤
ት.ሆሴዕ ፲፩÷፩

# ስምዐ ጽድቅ



## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ ርእሰ አንቀጽ
፯ ሪፖርታዥ
፲ ቤተ አብርሃም
፲፭ ቃለ መጠይቅ
፲፰ የሕፃናት ዓምድ
፳ ትዝብት
፳፪ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ



## ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በየወሩ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
Simatsidk12@gmail.com

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ረቂቅ መቻል
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ

# ከኃያላን መሪዎች የሚሰነዘረውን የጥፋት ጥሪ መመከት እንደሚገባ ቅዱስ ሲኖዶስ አሳሰበ

በካሣሁን ለምለሙ



*ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት*

ከኃያላን መሪዎችም ሆነ ከሌሎች ሀገራት የሚሰነዘረውን የጥፋት ጥሪ በአንድነት በመከባበርና በመመካከር መመከት እንደሚያስፈልግ ቅዱስ ሲኖዶስ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ አሳሰበ።

ቅዱስ ሲኖዶስ መግለጫውን የሰጠው ጥቅምት ፲፫ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም የአሜሪካው ፕሬዚደንት ዶናልድ ጄ ትራንፐ በኢትዮጵያ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን አስመልክቶ ሀገራትን ወደ ግጭትና አለመግባባት ውስጥ የሚያስገባ የጥፋት መልእክት ማስተላለፋቸውን ተከትሎ ነው።

የዶናልድ ትራፐን ግጭት ቀስቃሽ መልእክት በሐዘን እንደተመለከተው ቅዱስ ሲኖዶስ አስታውቆ ኢትዮጵያ በዘመናት ውስጥ ታፍራና ተከብራ የኖረችና ለመላው ጥቁር ሕዝብ ምሳሌ የሆነች ሀገሪቱ ሀገረ እግዚአብሔር ሕዝቡ ደግሞ ሕዝበ እግዚአብሔር በመሆኑ ነው ሲል በመግለጫው አስታውሷል።

ከአሜሪካው ፕሬዚደንት ዶናልድ ትራምፕም ሆነ ከሌሎች ተመሳሳይ አካላት በሀራችን ላይ እየተላለፈ ያለው የጥፋት ጥሪ መተዛዘቢያ ከመሆኑ በቀር ሀገራችን ጠባቂዋ በሆነው እግዚአብሔርና በሕዝቦቿ አንድነት ተከብራና ተጠብቃ ትኖራለች ሲል ቅዱስ ሲኖዶስ አስገንዝቧል።

ዶናልድ ትራምፕ በሀገራችን ላይ ያስተላለፉትን የጦርነት ጥሪ ቅዱስ ሲኖዶስ አጥብቆ እንደሚቃወመው ገልጦ መላው የዓለም መንግሥታትና ሕብረተሰብ ችግሩን በጥልቀት እንዲገንዘቡ አሳስቧል።

ሀገርን የመምራት ኃላፊነት የተሰጣቸው የፌዴራልና የክልል መሪዎች እንዲሁም ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የግልና የቡድን አመለካከቶችን ወደጎን ትተው አንድነታቸውን አጠናክረው ለሀገራቸው ህልውና ዘብ እንዲቆሙ ቅዱስ ሲኖዶስ በመግለጫው ጥሪውን አስተላልፏል።

# በቤተክርስቲያንና ''በኦሮምያ ቤተ ክህነት አደራጅ ኮሚቴ'' መካከል የነበረው ልዩነት በእርቅ መፈታቱን የተመለከተ መግለጫ ተሰጠ

በካሣሁን ለምለሙ

በቤተክርስቲያንና ‹‹በኦሮምያ ቤተ ክህነት አደራጅ ኮሚቴ›› መካከል ተፈጥሮ የቆየውን ልዩነት በእርቀ ሰላም መፍታቱን አስመልክቶ ጥቅምት ፲፱ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በጠቅላይ ቤተ ክህነት ‹‹ጽርሐ ተዋሕዶ›› አዳራሽ የጋራ መግለጫ ተሰጥቷል፡፡



ላእከ ሰላም ባያብል ሙላቴ



ሊቀ አእላፍ ቀሲስ በላይ መኰንን

‹‹የኦሮምያ ቤተ ክህነት አደራጅ ኮሚቴ” ሰብሳቢ ሊቀ አእላፍ ቀሲስ በላይ መኰንንና የሽማግሌ ቡድኑ ሰብሳቢ ላእከ ሰላም ባያብል ሙላቴ መግለጫውን በጋራ የሰጡ ሲሆን በኦሮምያ ክልል ያለችው ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መዳከም ያሳሰባቸው ወገኖች ችግሩን ለመፍታት ሲሉ ‹‹የኦሮምያ ቤተ ክህነትን›› ለማቋቋም እንቅስቃሴ ሲያደርጉ እንደቆዩ በመግለጫው ተነስቷል፡፡

“የኦሮምያ ቤተ ክህነት” ይዟቸው የተነሳው የአገልግሎት ችግሮች በአብዛኞቹ አባቶች፣ ሊቃውንትና ምእመናን የታመነባቸው ቢሆንም “"የኦሮምያ ቤተ ክህነትን”

ማቋቋም መፍትሔ ይሆናል የሚለው አሳብ ግን በቤተ ክርስቲያንና በአደራጅ ኮሚቴው መካከል ከፍተኛ ልዩነት ፈጥሮ እንደቆየ ከመግለጫው ለመረዳት ተችሏል፡፡

ልዩነቱን ለማጥበብና በመካከላቸው ያለውን ችግር ለመፍታት በአደራጅ ኮሚቴውና በሽማግሌዎቹ መካከል ላለፉት ስድስት ወራቶች ውይይቶች ሲካሄዱ እንደነበር በመግለጫው የተመለከተ ሲሆን ለስኬታማነቱም የሽማግሌ ቡድኑ “የኦሮምያ ቤተ ክህነት አደራጅ” አመራሮችን፣ ቋሚ ሲኖዶስንና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን እንዳነጋገረ ተገልጿል፡፡

በቀጣይም በኦሮምያ ክልል ያጋጠመውን የአገለግሎት መዳከም ለማሻሻል በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥር የሚቋቋም አካል ተጠናክሮ በአንድነት መሥራት የሚችልበትን ሂደት መፍጠር የተሻለ መሆኑ እንደታመነበት በመግለጫው ተነስቷል፡፡ ቅዱስ ሲኖዶስ በወሰነው መሠረትም በኦሮምኛ ቋንቋ የሚሰጠውን አገልግሎት በተጠናከረ መልኩ ለማከናወን ሁሉም የቤተ ክርስቲያኗ ባለድረሻ አካላት አንድ ሆነው እንዲሠሩም ጥሪ ቀርቧል፡፡



*የአሜሪካ ኦርቶዶክሳያን ጳጳሳት ኅብረት አባላት*

# በአሜሪካ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ጳጳሳት ኅብረት በጋራ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ አሳለፈ

በአሜሪካ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ጳጳሳት ኅብረት በኦርቶዶክሳዊ አንድነትና አገልግሎት ተደራሽነት ላይ በጋራ ለመሥራት ተስማምተው ውሳኔ ማሳለፋቸውን ኦርቶዶክስ ኦግኔት ፔጅ ዘግቧል።

በአሜሪካ የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናንን መንፈሳዊ ፍላጎትን ለማሟላት ሃይማኖታዊ ሥርዓትና አገልግሎት እንዲፈጸም ለማድረግ ኅብረቱ ውሳኔ ያሳለፈ ሲሆን ውሳኔውም በጋራ ተፈጻሚነት እንደሚኖረው ከዘገባው ለመረዳት ተችሏል።

የአሜሪካ ኦርቶዶክሳውያን ጳጳሳት ኅብረት ም/ኃላፊ ሜትርፓሊቲያን ዮሴፍ ፳፻፲፫ ዓ.ም ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች በትክክለኛ መንፈሳዊ ሕይወትና መስመር የሚገኙበት ማድረግና የኅብረቱ የጋራ እቅድ የሚፈጸምበት ዓመት ይሆናል በማለት እንደተናገሩ ዘገባው አመልክቶ ‹‹ወጣቶች የእኛ የዛሬና የወደፊቶች ናቸው›› ሲሉ አክለው እንደተናገሩም አስረድቷል።

የጳጳሳቱ ኅብረት ባካሄደው ጉባኤ የተመሠረቱ አዳዲስ ኦርቶዶክሳዊ ማኅበራት ሲኖሩ እነዚህም የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበርና የኦርቶዶክሳውያን በጎ አድራጎት ማኅበር ናቸው። እነዚህ ማኅበራት በልዩ ልዩ ኦርቶዶክሳዊ የአገልግሎት ዘርፍ በ፳፻፲፫ ዓ.ም ወደ ሥራ እንደሚገቡም ከዘገባው ለመርዳት ተችሏል።

ማኅበራቱ የኦርቶዶክሳውያን ወጣቶችን መንፈሳዊ ሕይወት የመቅረጽ ሥራ የሚያከናውን ሲሆን ያለውን አቅምና የፈጠራ ችሎታ በመጠቀም የሚሠራ ይሆናል ተብሏል። የጳጳሳት ኅብረቱ በማኅበራቱ ቆይታ ላይ የጊዜ ገደብ ያስቀመጠ ሲሆን ይህም የማኅበራቱን ጥልቀትና ተቀባይነት ለማረጋገጥ ይጠቅማል ሲል ዘገባው አስረድቷል። ዓመታዊ ኦርቶዶክሳዊ ጉባኤ እንዲሁም የወጣቶች ሠራተኛ ጉባኤ በዚሁ ዓመት እንዲካሄድ መወሰኑንም ለመረዳት ተችሏል።

# ቤተ ክርስቲያንን ለመታደግ የውስጥ ልዩነትን ማስወገድ ይገባል

የ፳፻፲፫ ዓ.ም ፴፱ኛ የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ በሀገሪቱ ላይ የመጣውን የመንግሥት ለውጥ ተከትሎ እንዲሁም በየጊዜው ሲከሰቱ የነበሩና ከቤተ ክርስቲያን ጋር ምንም ግኑኝነት የሌላቸውን ሁነቶች መነሻ በማድረግ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የጥቃት ዒላማ ሆና መቆየቷን አስረድቷል፡፡ በሀገሪቱ ውስጥ በተለያዩ ሀገረ ስብከቶች በምእመናን ሕይወት እና ንብረት ላይ፣ በአገልጋይ ካህናት እና በቤተ ክርስቲያን የደረሰው መጠነ ሰፊ ጉዳት ታሪክ የማይረሳ መሆኑን ገልጿል፡፡

በተለይም በኦሮሚያ እና በደቡብ ክልሎች በሚገኙ ሀገረ ስብከቶች ኦርቶዶክሳውያን ላይ የደረሰው ዘርፈ ብዙ ጥቃት እና ውድመት ፣ በንብረት እና በሕይወት ላይ የደረሰው ጥፋት ከዚህም ባሻገር ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ስትጠቀምባቸው የነበረውን የአደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎች ንጥቂያ ብሎም በዓላቱ እንዳይከበሩ የተፈጠሩ አሉታዊ ተጽእኖዎች ብዙዎችን ሲያነጋግር የሰነበተ አሁንም ድረስ እያነጋገረ ያለ ዐቢይ ጉዳይ ነው፡፡

በቤተ ክርስቲያኒቱ እና በተከታይ ምእመናንዋ ላይ እየተካሄደ ያለው የጥፋት ዘመቻ በአካራሪ ኃይል፣ በአፅራረ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ሀገርን እንደ ሀገር እንድትቀጥል ትልቁን ድርሻ የያዘችውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የማጥፋት ዋና ተልእኮዋቸው አድርገው በተነሱ አንዳንድ የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያሉ ባለስልጣናት አማካይነት አንዳንዴ በድብቅ ሌላ ጊዜ ደግሞ በግልጽ ሲካሄድ መቆየቱ የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡

ብዙ የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች፣ ካህናት እና ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጉዳዩን ከሥር ከሥር እየተከታተሉ ግድያውን፣ የንብረት ውድመቱን፣ ዝርፊያውን እና ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የማጥፋት ዘመቻ ሲቃወሙ፣ ሲያወግዙ እንዲሁም ሀገሪቱን ለሚመራው የበላይ አካል በመረጃ የተደገፈ አቤቱታቸውን ሲያቀርቡ ቆይተዋል፡፡ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ እየተቃጣ ያለው የጥፋት ዘመቻ ከመቀነስ ይልቅ እየባሰ መምጣቱን ከዳር ሀገር ወደ መሀል መግባቱ እታየ ነው፡፡

ይህ በተቀናጀ መልኩ እየተካሄደ ያለ የጥፋት ተልእኮ በተለይም ወቅት ጠብቆ፣ ምክንያት ፈልጎ፣ አሳቻ ጊዜን ተገን አድርጎ በኦርቶዶክሳውያን

ላይ እየተፈጸመ ያለውን ዘመቻ ለመከላከል፣ ለተጎዱት ለመድረስ ብዙዎች በግልም በማኅበርም ከሀገር ውስጥ እስከ ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ሲረባረቡ ቆይተዋል፡፡ በተለያየ ጊዜም የተቃውሞ መግለጫ፣ ማሳሰቢያ፣ ሲሰጥ መቆየቱ አይዘነጋም፡፡

ተጎጅዎችን ምስክር ያደረገ ጥፋት እና የጉዳት ጥልቀት በተለያዩ ጊዜያት ወደ መንግሥት እና የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ደርሰዋል፣ በየሀገረ ስብከቱ ያሉ ሊቃነ ጳጳሳት የጥፋት ዘመቻውን ስፋት፣ ከጥፋት ዘመቻው ጀርባ ያሉትን ስውር አንጀንዳዎች እና እቅዶች፣እንዲሁም በዚህ ሁሉ ጥፋቶች ውስጥ መንግሥት ያሳየውን ቸልተኝት ጭምር በግልጽ ተችተዋል፡፡

ይህ እየተጠራቀመ፣ በላይ በላይ እየተደራረበ፣ የመጣው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የማዳከም ብሎም የማጥፋት ዘመቻ ከቃል፣ ከውግዘት፣ ከማሳሰቢያ፣ ከማስጠንቀቂያ እና ከቃላዊ ተቃውሞ ያለፈ እና መሬት ላይ የወረደ ሥራ ያስፈልገዋል፡፡ ኦርቶዶክሳውያን ተደራጅተው ራሳቸውን መጠበቅ አለባቸው የሚለው የቅዱስ ፓትርያርኩ የ፴፱ኛው አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ መክፈቻ መልእክት መዋቅሩን ጠብቆ በተግባር የተገለጠ የተደራጀ ኃይል ኑሮት ከመልእክትነት ያለፈ ቁም ነገር ሊኖረው ይገባል፡፡

በቤተ ክርስቲያኒቱ እና በቤተ ክርስቲያኒቱ ሥር ባሉ ተቋማት በተለያየ ጊዜ የወጡ የአቋም መግለጫዎች፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን መብትና ጥቅም ሊያስከብሩ ይገባል የሚሉ ጥብቅ ማስጠንቀቂያዎች ከወረቀት ባለፈ መሬት ላይ ወርደው ተግባራዊ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ባለፉት ሦስት ዓመታት ብቻ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ከደረሱት ዘርፈ ብዙ ጥቃቶች ጋር ተያይዞ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ግለሰቦች፣ ማኅበራት አባቶች እና በቤተ ክርስቲያኒቱ ተቋማት የአቋም መግለጫዎች መውጣታቸው፣ የተለያዩ ማሳሰቢያዎች መተላለፋቸው ይታወቃል ሆኖም ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ እየተቃጣ ያለውን ጠንካራ የጥፋት ዱላ መመከት አልተቻለም፡፡ ለዚህ ማሳያው ደግሞ የአቋም መግለጫዎቹ፣ ማስጠንቀቂያዎቹና ማሳሰቢያዎቹ በተላለፉ ማግስት የጥፋት ዘመቻው በእጥፍ መጨመሩ ነው፡፡

በመሆኑም ሁሉም የሚመለከተው የቅድስት ቤተ ክርስቲያን አካል ከቅዱስ ሲኖዶስ ጀምሮ እስከ ምእመናኑ ድረስ በ፴፱ኛው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ለተላለፉት ውሳኔዎች ተግባራዊነት የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በዚህ ወቅት በኅብረት መቆም፣ በተለይም የውስጥ ልዩነትን አስወግዶ ባንድ ሐሳብ በመቆም ቤተ ክርስቲያንን በዘላቂነት ከጥቃት የመከላከል ሥራ ሊሠራ ይገባል፡፡

# የአደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታን በመንጠቅ በዓላቱን የማደብዘዝ ድብቅ ሴራ

በካሣሁን ለምለሙ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአደባባይ ከምታከብራቸው ዐበይት በዓላት መካከል የጥምቀትና የመስቀል ደመራ በዓላት በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው። ቤተ ክርስቲያኗ እነዚህን የአደባባይ ሕዝባዊ በዓላት ሃይማኖታዊ ሥርዓቱ እንደተጠበቀ ከዘመን ዘመን ስታከብር ቆይታለች። በእነዚህ የአደባባይ በዓላት አማካይነት ቤተ ክርስቲያኗ ሃይማኖታዊ ሥርዓቷን ለመላው ዓለም ከማስተዋወቅ አልፋ የሀገርን ባህልና ዕሴት ማሳየት ችላለች። ከዚህም ባሻገር ለሀገራችን ኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የገቢ ምንጭ ሆናለች። በዓላቱን ለመታደም ከተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚመጡ ዜጎች በሀገራችን በሚኖራቸው ቆይታ የሚገኘው ገቢ ከዕለት ዕለት እየጨመረ መምጣቱን ማስተዋል ይቻላል።

ከተለያዩ ዓለማት የሚመጡ ዜጎችም በሚያዩት ሃይማኖታዊ ሥርዓት ተደስተው ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ የቤተ ክርስቲያኗን ሥርዓትና ሀገሪቱን ለወዳጅ ዘመዶቻቸው ያስተዋውቃሉ። በዚህም በየዓመቱ በዓላቱን ለመታደም የሚመጡት የውጭ ሀገር ዜጎች ከጊዜ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረ መጥቷል። ይህንን የተመለከተውና የበዓላቱን ሃይማኖታዊ ሥርዓት በደንብ የገመገመው ዩኒስኮ የጥምቀትና የመስቀል ደመራ በዓላት የዓለም ቅርስ ሆነው እንዲመዘገቡ አድርጓል። በዓላቱ በዩስኮ ከተመዘገቡ በኋላም የጎብኝው ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። ይህም ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለሀገር ሁለተናዊ ጥቅም ፈጥሯል ማለት ይቻላል።

በዓላቱ በሀገራችን ኢትዮጵያ በተለየ ድምቀት ከመከበራቸው ባለፈ ኦርቶዶክሳውያን ባሉበት የዓለም ክፍል ሁሉ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱ ተጠብቆ ይከበራሉ። አሁን ላይ በዓላቱ በሌላው ዓለም የሚከበሩትን ያህል በኢትዮጵያ በአንደንድ ቦታዎች በነጻነት እየተከበሩ ነው ለማለት አያስደፍርም። በዓላቱ በአንዳንድ የኢትዮጲያ ክፍሎች በሚከበሩበት ወቅት የበዓሉን ድባብ ለማበላሸት ፀረ ክርስቲያን ኃይሎች ሁልጊዜ ሁከትና ብጥብጥ ይፈጥራሉ፤ በታቦተ ሕጉ ላይ ድንጋይ ይወረውራሉ፤ የምእመናን ነጠላ ይነጥቃሉ፤ ያሳድዳሉ እንዲሁም "ታቦተ ሕጉ በእኛ አካባቢ አይሄድም" በማለትም መንገድ ይዘጋሉ። እነዚህ ሕገ ወጥ ድርጊቶች በአመዛኙ በድሬደዋ፣ በሐረር፣ በምዕራብ አሩሲና በባሌ አካባቢዎች ይስተዋላሉ።

በበዓላቱ ላይ እየተፈጸሙ የመጡ ትንኮሳዎች ተጠናክረው በመቀጠላቸው የመንግሥት ሹማምንቶች የመስቀልና የጥምቀት በዓላትን ማክበሪያ ቦታዎችን እስከመንጠቅ ደርሰዋል።

በተለይ በአሁኑ ወቅት በዩኒስኮ የተመዘገቡ የአደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎችን ያለአግባብ መንጠቅ የተለመደ ተግባር እየሆነ መጥቷል። በአንዳንድ የሀገራችን ክፍሎች የአደባባይ በዓላት ማክበርያ ቦታዎች እየነጠቁ ያሉት የበዓሉን ጥቅምና ጣዕም ያልተረዱ አንዳንድ የመንግሥት ሹማምንቶች እንደሆኑ ከኦሮሚያና ከደቡብ ክልሎች ምእመናን በኩል ከሚመጡ መረጃዎች መረዳት ይቻላል። የአደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎችን በተመለከተ በአብዛኛው ቅሬታ ከሚስተናገድባቸው ክልሎች መካከል የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥትና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በግንባር ቀደምነት ተጠቃሾች ናቸው።

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ከአንድም ሁለት የበዓላት ማክበሪያ ቦታዎችን የየአካባቢው የመንግሥት ኃላፊዎች እንደነጠቁ ከሀድያና ጋሞ ጎፋ አህጉረ ስብከት የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ። የሀድያ ዞን የመንግሥት አመራሮች ደግሞ የዚህ ተግባር ማሳያዎች ናቸው። የሀድያ ዞን የመንግሥት አመራሮች ሕዝብና

መንግሥት የሰጣቸውን ኃላፊነት ወደጎን ትተው ‹‹የእኔ›› ለሚሉት የሃይማኖት ተቋም በመሥራታቸው የተነሳ ኦርቶዶክሳውያን ለረጅም ዘመናት የአደባባይ በዓላትን የሚያከብሩባቸውን ይዞታዎች እንደተነጠቁ የሀገረ ስብከቱ ሊቀጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ በቅርቡ በመግለጫቸው ማስረዳታቸው ይታወቃል፡፡

በሆሣዕና ከተማ አስተዳደር የሚገኘው ‹‹ጎፈር ሜዳ›› የተባለውን የጥምቀትና የመስቀል በዓላት ማክበሪያ ቦታ የመንግሥት አካላት መንጠቃቸውን ተከትሎ የአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን በዓላቱን ማክበሪያ ቦታ ከማጣታቸው ባለፈ ለከፍተኛ ሥነ ልቡናዊ ጫና እየተዳረጉ እንደሆነ ብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ ለመገናኛ ብዙኃን በሰጧቸው መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡ አንዳንድ የዞኑ የመንግሥት ባለሥልጣናትም ለቤተ ክርስቲያኗ ካላቸው ጥልቅ ጥላቻ የተነሳ ቤተ ክርስቲያኗ ያነሳችውን የይዞታ ይገባኛል ጥያቄ ከመመለስ ይልቅ ‹‹ወራሪ›› እያሉ መሳደብ የሚቀናቸው እንደሆኑ ብፁዕነታቸው በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ተናግረዋል፡፡ የተጠየቀውን ጥያቄ በአግባቡ መመለስ ተገቢ ሆኖ ሳለ የሕዝበ ክርስቲያኑንና የቤተ ክርስቲያንን መብት በኃይል በመጨቆን በሕዝቦችና በመንግሥት መካከል መጠራጠር፣ ግጭትና ሁከትን ለመፍጠር የሚተጉ የዞኑ አመራሮች እየተከራከቱ መምጣታቸውንም ከብፁዕነታቸው ንግግር መረዳት ይቻላል፡፡ እስከአሁን ድረስ በሀድያ ዞን ሆሣዕና ከተማ የአደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታ ችግር እንዳልተፈታ ይታወቃልና የቤተ ክርስቲያኗንና የአካባቢውን ምእመናን ጥያቄ በአግባቡ መመለስ ካልተቻለ ለሀገር አንድነትም ሆነ ሰላም እንቅፋት መሆኑን መርዳት ያስፈልጋል፡፡

በሀድያ ዞን በሆሣዕና ከተማ አስተዳድር ያለው ችግር መፍትሔ ሳያገኝ በጋሞ ጎፋ ሀገረ ስብከት በመሎ ኮዛ ወረዳ የላሃ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ለ፶፫ ዓመታት ያህል ለአደባባይ በዓላት ማክበሪያ ሲጠቀሙበት የነበረውን ቦታ የወረዳው የመንግሥት ኃላፊዎች መንጠቃቸውን የመሎ ኮዛ ወረዳ ቤተ ክህነት ያወጣው መረጃ ያመለክታል፡፡ በዚሁ ሀገረ ስብከት የሚገኘውን የጥምቀትና የመስቀል በዓላት ማክበሪያ ቦታን የወረዳው የመንግሥት ኃላፊዎች ያለአግባብ መንጠቃቸውን አስመልክቶ የአካባቢው ምእመናን ድርጊቱን በማውገዝ ከወረዳ እስከ ፌዴራል መንግሥት አቤቱታ ያቀረቡ ፳፪ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን ያለ አግባብ በእስርና በገንዘብ ተቀጥተዋል፡፡ በሐሰት ክስ ከ፯-፱ ዓመታት ከመታሰራቸው ባለፈ በእያንዳንዳቸው ላይ የተወሰነ መቀጮ በአጠቃላይ ሲደመር ፪፻፱ ሺህ ፭፻ ብር ሲሆን የእስር ትእዛዙም ሆነ የብር መቀጮው ተፈጻሚ ሆኖ የሐሰት ክስ የቀረበባቸው ምእመናን በአሁኑ ሰዓት በእስር ላይ እንደሚገኙ የመሎ ኮዛ የወረዳ ቤተ ክህነት ለዝግጅት ክፍላችን የላከው መረጃ ያሳያል፡፡

በጋሞ ጎፋ ዞን በመሎ ኮዛ ወረዳ የአደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታ ላይ በመንግሥት ኃላፊዎች አማካይነት እየተፈጸመ ያለውን ግፍና በደል የወረዳው ቤተ ክህነት በቀን ፲፪/፲፩/፳፻፲፩ ዓመተ ምሕረት በጻፈው ደብዳቤ በዝርዝር ለሀገረ ስብከቱ ማሳወቁን ተከትሎ የጋሞ ጎፋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ አቤቱታቸውን ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት አስተላልፈዋል፡፡ ጠቅላይ ቤተ ክህነቱም በቅዱስ ፓትርያርኩ በኩል በተጻፈ ደብዳቤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዶክተር ዐቢይ አሕመድ መመሪያ እንዲሰጡ ቢጠየቁም እስካሁን ድረስ ምንም ዓይነት ውሳኔ ሳይሰጡ በመቅረታቸው ድርጊቱን የተቃወሙ ከ፳፪ በላይ ንጹሓን ምእመናን ለከፍተኛ እስር፣የገንዘብ መቀጮና እንግልት ተዳርገዋል፡፡

ጉዳዩ ሳይጠነክርና ሳይከፋ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት በቀን ፪/፱/፳፻፲ ዓመተ ምሕረት በጻፈው ደብዳቤ የምእመናኑ ጥያቄ እንዲመለስና የሃይማኖት ነጻነት እንዲረጋገጥ ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ቅሬታውን አሰምቷል፡፡ ይህ ሁሉ ሕጋዊ መንገድ ታልፎም ታድያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ በተለያየ የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ የመንግሥት ሠራተኞች “ሃይማኖታችሁን ደግፋችኋል” በሚል ሰበብ ደምወዛቸውን መቁረጥ፣ የትምህርት እድል ውድድር መከልከል እንዲሁም ሃይማኖታቸውን ለማስለወጥ እንቅስቃሴ እያደረጉባቸው ነው ሲሉ የጋሞ ጎፋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ በቀን ፲፯/፫/፳፻፲፩ ዓመተ ምሕረት ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ርእሰ መስተዳድር ጽ/ቤት በጻፉት ደብዳቤ

አሳውቀዋል፡፡ በመሆኑም የክልሉ መንግሥት ጉዳዩን በአግባቡ ተረድቶ የምእመናንን ጥያቄ በመመለስ ምእመናኑ በቀድሞ ቦታቸው የመስቀልና የጥምቀት በዓላትን በነጻነት እንዲያከብሩ እንዲደረግ በደብዳቤ ጠይቀዋል፡፡

ምእመናኑ ተከሰው በፍርድ ቤት ቅጣት የተበየነባቸው ‹‹የበዓላት ማክበሪያ ቦታችን ለምን ይነጠቃል?›› ብለው በመጠየቃቸው ብቻ እንደሆነ የወረዳ ቤተ ክህነቱ አስታውቋል፡፡ በአንጻሩ በወረዳው የመንግሥት ኃላፊዎች በኩል በቀን ፲፰/፫/፳፻፲ ዓመተ ምሕረት በተጻፈ ደብዳቤ “ምእመናኑ የተከሰሱበት ለመናኸሪያ ተብሎ በተወሰነው ቦታ ላይ ሕገ ወጥ ግንባታ በመገንባታቸው ነው” ብለዋል፡፡ ምእመናኑ በተጠቀሰው ቦታ ሕገ ወጥ ግንባታ እንዳያከናውኑ ቢነገራቸውም እምቢተኛ በመሆን በኃይል ግንባታውን በማካሄዳቸው በክሱ መሠረት የእስራትና የገንዘብ መቀጮ እንደተጣለባቸው የክሱ ዝርዝርም ያስረዳል፡፡

> **ምእመናኑ ተከሰው በፍርድ ቤት ቅጣት የተበየነባቸው «የበዓላት ማክበሪያ ቦታችን ለምን ይነጠቃል?» ብለው በመጠየቃቸው ብቻ እንደሆነ የወረዳ ቤተ ክህነቱ አስታውቋል።**

ይሁን እንጂ በ፲፱/፲፩/፳፻፲፩ ዓመተ ምሕረት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ከጋሞ ሀገረ ስብከት የደረሳቸውን ቅሬታ ተቀብለው ለሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐብይ አህመድ የአቤቱታ ደብዳቤ አስገብተው ነበር፡፡ በደብዳቤውም በጋሞ ጎፋ ሀገረ ስብከት በመሎ ኮዛ ወረዳ አስተዳደር የሚገኘው የላሃ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ከ፶ ዓመታት በላይ ሲገለገሉበት የነበረውን የጥምቀትና የመስቀል ማክበሪያ ቦታ የመሎ ኮዛ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ለሌላ አገልግሎት በማዋሉ ማኅበረ ምእመናኑና ካህናቱ የይገባናል ጥያቄ በማንሳታቸው ለከፍተኛ እስራትና እንግልት እየተዳረጉ እንደሆነ በደብዳቤው አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም በጠቅላይ ሚኒስትሩ በኩል ታይቶ አመራር እንዲሰጥበት ቅዱስነታቸው ጠይቀው ነበር፡፡ በጉዳዩ ዙሪያ ምላሽ እንዲሰጡን የመሎ ኮዛ ወረዳን ፖሊስ አዛዥ ኢንስፔክተር ይስሐቅ ጨርጋ እና የወረዳውን አስተዳዳሪ አቶ ኤርምያስ ወሰንን የጠየቅን ቢሆንም ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ምላሻቸውን ማካተት አልቻልንም፡፡ ነገር ግን የወረዳውን የብልጽግና ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሰሎሞን ስባቱን አናግረን “ጉዳዩን በቅርበት እየተከታተልኩ ነው ወረዳው ከሕግ ውጭ የሆነ ሥራ እየሠራ ከሆነ አጣርተን **መፍትሔ** እንሰጣለን” የሚል ምላሽ ሰተውናል፡፡

ሁለቱ የአደባባይ በዓላት መከበራቸው ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በመገንዘብ መንግሥት የበዓላቱን ማክበሪያ ቦታዎች የይዞታ መብት ቢያረጋግጥ መልካም ነው፡፡ መንግሥት በመላ ሀገሪቱ ላሉ የአደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎች ለቤተ ክርስቲያኗ ሕጋዊ ሰነድ አዘጋጅቶ ሲሰጥ ሀገሪቱ ከብጥብጥና ሁከት ትድናለች፡፡ በዓሉን በዩኒስኮ ያስመዘገበው ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን ጠብቆ በመከበሩ ነውና የበዓላቱ ማክበሪያ ቦታዎች ሕጋዊ ከለላ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የቤተ ክርስቲያኗንና የምእመናንን ድምፅ መስማትም ተገቢ ነው፡፡ በየአካባቢው ያሉ የአደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎች ጥያቄ ያለመመለስ በሀገሪቱ ሰላምና ፍቅር እንዲሁም መረጋጋትን ስለማያመጣ መንግሥት ቆም ብሎ ሊያስብበት ይገባል እንላለን፡፡

# “የአብነት መምህራን ከሌሉ ከቤተ ክርስቲያን አልፎ የኢትዮጵያ ማንነት ያሰጋኛል”

**ክፍል አንድ**

በመጽሐፈ ሲራክ



መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ

*የተወደዳችሁ አንባብያን በዛሬው የቤተ አብርሃም ዓምድ ዝግጅታችን በደብረ ጽጌ ቅዱስ ኡራኤል ቤተ ክርስቲያን የአብነት መምህር የሆኑትን ታላቅ አባት ይዘንላችሁ ቀርበናል፡፡ አብዛኛውን የዕድሜያቸውን ክፍል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው ያሳለፉት በተማሪነት ከዚያም በአብነት መምህርነት መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ ተክሌ የተወለዱት ዋግ የሚባል አካባቢ ሰቆጣ ውስጥ ነው፡፡ ነጋ ለኪዳን መሸ ለቁርባን ሁል ጊዜ ታታሪ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ከነበሩት አባታቸው ቀሲስ ወልደ ተክለሃይማኖት እና ከእናታቸው አበባ ማርዋ መጋቢት ፳፫ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ.ም ተወለዱ፡፡ መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከዚያው የተወለዱበት አካባቢ ደብረ ሰላም በለዛ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከቀኝ ጌታ ተኮላ ዘንድ ከፊደል እስከ መዝሙረ ዳዊት ፤ ከግብረ ዲቁና አልፎ አርያም ሠልስቱን ተምረዋል፡፡ አሁን በደብረ ጽጌ ቅዱስ ኡራኤል ቤተ ክርስቲያን የቅኔ መምህር ናቸው፡፡ በቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ዘመናቸው ውስጥ ከልጅነት እስከ እውቀት ያለፉበትን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲያካፍሉን ጠይቀናቸው እንደሚከተለው ነግረውናል፡፡*

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በአብነት ትምህርት ቤት እስከምን ድረስ የት የት አካባቢ ተዘዋውረው ተማሩ?

***መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ፦*** መጀመሪያ የተማርኩበትን አካባባቢውን ለቅቄ ለመማር ከወጣሁ በኋላ ዝቋላ ወረዳ ውስጥ ከምትገኘው ዲስቁ ማርያም የኔታ መኮንን ከሚባሉ የቅኔ መምህር ዘንድ ነው የሄድኩት፡፡ የኔታ መኮንን ፪፻ የሚደርሱ ተማሪዎች ነበሯቸው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ቅኔ የተቀኘሁት ከእርሳቸው ዘንድ ነበረ፡፡ ሰምና ወርቅ ጥሩ ችሎታ ነበራቸው፡፡ የኔታ መኮንን ከጊዜ በኋላ ላሊበላ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን የቅኔ መምህር ሆነው ተቀጥረው ብዙ ዘመን አገልግለዋል፡ ገድለ ላሊበላን ከግዕዝ ወደ አማርኛ የተረጎሙትም እሳቸው ናቸው፡፡ ከእርሳቸው ዘንድ ከተማርኩ በኋላ ወደ ሰቆጣ ከተማ ሄጄ ደብረ ገነት መድኃኔ ዓለም ደብር ከሚገኙት የመጻሕት እና የቅኔ መምህር ከሆኑት ባሕታዊ አባ ዓለሙ ዘንድ ቅኔን ከነአገባቡ በሚገባ ቀጸልኩ፡፡

ከዚያ መልስ ወደ ዳሃና ዓምደ ወርቅ ልዩ ቦታው ጉራምባ ጊዮርጊስ በመሄድ የኔታ ታምራት ከሚባሉ ሊቅ ዘንድ ዝማሬ መዋሥዕት፣ ጾመ ድጓ፣ ድጓና ምዕራፍን ተምሬአለሁ፡፡ በኋላም ወደ ናአኵቶ ለአብ በመሄድ የድጓና የቅኔ መምህር ከሆኑት የኔታ ኃይለ ማርያም ቅኔውን አጠናቀቅሁ፡፡

ከየኔታ ኃይለ ማርያም ዘንድ ቅኔውንና ዜማውን ካጠናቀቅሁ በኋላ ዓይኔን ታምሜ ስለነበር ቦሩ ሜዳ የዓይን ሐኪም አለ ስለተባለ አባቴ ከሳስታ ወደ ዋድላ ደላንታ ይዞኝ መጣ። ቦሩ ሜዳ (ከደሴ ከተማ ወጣ ያለ ነው) ስንደርስ ግን ሐኪሙ ለዓመት ስለቀጠረን አባቴ ወደ ሀገሩ ሲመለስ እኔ ህክምናውን መጠበቅ ስለነበረብኝ ደሴ ውስጥ ደብረ ቤቴል ሥላሴ ከየኔታ ዕንቁ ባሕርይ (መምህር ኃይለ ማርያም) ዘንድ ትምህርት ቤት ቀረሁ። መምህር ኃይለ ማርያም አራቱ አይናማዎች ከሚባሉት አንዱ ናቸው። አራቱ አይናማዎች ዓይነ ስውሮች ናቸው። አራቱም በአንድ ወቅት የወጡ የቤተ ክርስቲያን ዕንቁ ሊቃውንት ነበሩ። እኔም የሕክምናዬን ቀጠሮ እየጠበቅሁ እሳቸው ዘንድ ክብረ በዓልን፣ወርኀ በዓልን ተማርኩ። ከዚያም ደሴ ከተማ ውስጥ ከነበረው አዳሪ ትምህርት ቤት ገብቼ ትርጓሜ ሐዲሳትን ተማርኩ።

በዚያው በትምህርት ላይ እንዳለን ወቅቱ ፲፱፻፸፯ ዓመተ ምሕረት ደሴ ላይ ረኀብ ጸንቶ ነበርና መምህራችን የኔታ ዕንቁ ባሕርይ ከዚህ ከከተማው ገጠሩ ይሻላል ወደ ኤልሻማ መድኃኔ ዓለም ሄዳችሁ ብትማሩ ጥሩ ነው ብለው ደብዳቤ ጻፉልን። እኔ ከሌሎቹ ትንሽ ከፍ እል ነበርና የሰጡኝን ደብዳቤ ይዤ ስድስት ተማሪዎችን አስከትዬ ቅኔውንም አቋቋሙንም እያስቀጸልኩ ወደ ኤልሻማ መድኃኔ ዓለም ስንጓዝ ያገኙኝ ገበሬዎች መንገድ ለመንገድ /አስፋልቱን/ ስትሄድ ጓደኞችህን ደርግ ይነጥቅህና ብቻህን ትቀራለህ አንተ ደካማ ነህ ወደዚህ ወደ ገጠሩ ነው እንጂ ወደ ኤልሻማ መድኃኔዓለም አስፋልቱን አትሂዱ ብለው ወደ አማራ ሳይንት እንድመለስ ነገሩን። በጊዜው መምህር ዕንቁ ባሕርይ ያዘዙንን ትተን ወደ አማራ ሳይንት ወደ ላይ ሄድን። አማራ ሳይንት የኔታ መንግሥቱ የሚባሉ የአቋቋም መምህር ነበሩና ከእርሳቸው ዘንድ ገባን ሆኖም ወቅቱ የረኀብ ነበርና ከዚያም የጠበቀን የከፋ ችግር ነበር።

ከዚያ ብዙም ስላልተመቸን በሽሎውን ተሻግረን ስማዳ ከተማ ጃምባ ተክለ ሃይማኖት የተክሌ አቋቋም መምህር ከነበሩት ከየኔታ ኪዳነ ማርያም ዘንድ ለመማር ገባን። እኔ የተማርኩት ጎንደሬ ነው እሳቸው ደግሞ ተክሌ ስለሆኑ በጊዜው መግባባት አልቻልንም። ብዙም ሳንቆይ መምህራችን የኔታ ኪዳነ ማርያም "ስለተጠራሁ ወደ ወለጋ ልሄድ ነውና ደብረ ኤልያስ ጠብቁኝ" ብለው ደብዳቤ ጽፈው ሰጡን። እንደገና ስድስቱን ጓደኞቼን እንደያዝኩ የአባይን በረሃ በእግራችን ተያያዝነው። ከወንዙ ስንደርስ ውሃው ከብብታችን እየደረሰ መሻገር አቅቶን ነበር ሆኖም እንደምንም በአካባቢው የነበሩ ዋናተኞች አሻግረውን ደብረ ወርቅ ጉንደ ወይንን አልፈን ደብረ ማርቆስ ደረስን። መምህራችን ያዘዙን ደብረ ኤልያስ እንድንጠብቃቸው ቢሆንም በየመንገዱ የሚያገኘን ሰው ሁሉ ሲጠይቀን "ክህነት ልንቀበል ነው" እያልን አልፈናቸው እንሄድ ነበር።

ደብረ ማርቆስ ደርሰን ደኅና የቅኔ መምህር መፈለግ ጀመርን። የሚያስተምረን ደኅና የቅኔ መምህር እንፈልጋለን የት እናገኛለን ብለን ሰዎችን ስንጠይቅ መምህር ጥበቡ ደስታ የሚባሉ ሊቅ በደንበጫ (ከደብረ ማርቆስ ወጣ ያለች ትንሽ ከተማ) አሉ ብለው ስለጠቆሙን ፈልገን ከየኔታ ጥበቡ ዘንድ ገባን። በዚያም የጎንጅ ቅኔ፣አገባብ እርባ ቅምር ተምሬ የምስክር ወረቀት ተቀብያለሁ። ከዚህም በተጨማሪ ዋሸራውን ወደ ጎንጅ እየገለበጥኩ ብዙ ጊዜ በተማሪነት የኖርኩ ከእርሳቸው ዘንድ ነው። ዋናው መምህሬ እርሳቸው ናቸው ማለት ነው።

***ስምዐ ጽድቅ ፦*** በቀሰሙት የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የት የት አካባቢ ተዘዋውረው አገለገሉ?

***መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ፦*** እንደሚታወቀው ተማሪ ትምህርት ቤት ገብቶ የቤተ ክርስቲያኒቱን ዕውቀት ለመቅሰም ፴ እና ፵ ዓመት ይማራል የሚያገለግለው ግን ውስን ነው በትምህርት ቤት የሚያሳለፈው ጊዜ ይበልጣል። በአገልግሎቱም ጠንካራም ደካማም ጎን ሊኖረው ይችላል። እኔ ከየኔታ ጥበቡ አስተምር ተብዬ የምስክር ወረቀት ከተቀበልኩ በኋላ አቋቋም ለማስመስከር እፈልግ ስለነበር ወደ ጎንደር ነው የኼድኩት። ለተወሰነ ጊዜ ገጠር አስተምሬ አዘዞ ተክለ ሃይማኖት አካባቢ ማርያም ደብር የምትባል አለች እዚያ የኔታ ኤርምያስ ጋር የተወሰነ ጊዜ ቆየሁ። ብዙ ተማሪዎች ስለነበራቸው ብዙም አልተመቻቸልኝም እንደገና ወደ ጎንደር ተመልሼ አዘዞ አቢየ እግዚእ ኪዳነ ምህረት ደብር ነው የገባሁት። በዚያ የነበሩት መምህር የኔታ አክሊሉ ይባላሉ የአቋቋም መምህር ናቸው እሳቸውእሳቸው ጋር ተጠግቼ እየተማርኩ ሳለ

የደብሩ አለቃ አለቃ ገዳሙ ይባላሉ ፶ ብር እንክፈልህና ቅኔ አስተምር ስላሉኝ  አቢየ እግዚእ ኪዳነ ምሕረት ቀን ቀን እያስነገርኩ ማታ ማታ ቅኔ እየዘረፍኩ ብዙ ተማሪዎች አስተምሬአለሁ፡፡ በዚያ ቅኔ ብቻ ሳይሆን አቋቋምም አስተምር ነበር፡፡ በደብሩ መምህር አክሊሉ እና መምህር ዳዊት  የሚባሉ በአካባቢው የሚያስተምሩ በአንድ ደብር ሁለት የአቋቋም መምህራን ነበሩ፡፡ እኔም በዚያ ተቀምጬ እያስተማርኩ ያልተማርኩትንም እማር ነበርና ብዙ ጥቅም አግኝቼበታለሁ፡፡

ከዚያ በኋላ አቋቋም አስመሰክራለሁ ብዬ  ከየኔታ ሄኖክ (መጋቤ አዕላፍ)  አሰፈቅጄ ነበረ ነገር ግን ወንበር ተይዞአል ስለተባለ ወንበር አላገኘሁም እንዲሁ በተመላላሽ ከእርሳቸው እማር ነበረ፡፡ እንግዲህ በዚያ ዘመን የተወሰነ ጊዜ አስተምሬ ነበር ፡፡

> እነዚህ አሁን የቆጠርኳቸው ማሠልጠኛዎች የቤተ ክርስቲያኒቱ አንደበቶች ነበሩ፡፡ ዛሬ እነርሱ ቢኖሩ ኖሮ ቤተ ክርስቲያን ባልተቃጠለችም ነበር መናፍቃንም ባልበዙ ነበር፡፡

***ስምዐ ጽድቅ ፦*** ከጎንደር ወደ አዲስ አበባ እንዴት ሊመጡ ቻሉ?

***መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ፦*** አጋጣሚ ሆኖ መምህር ሰሎሞን የሚባል ቅኔ ቤት አብረን የነበርን ጓደኛዬ ቀደም ብሎ አዲስ አበባ መጥቶ መንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ማርያም በቅኔ መምህርነት ተቀጥሮ ነበረ፡፡ ወደ እኛ መጥቶ በተገናኘን ጊዜ አዲስ አበባ ለመምጣት ፈልጋለሁና እባክህ ቦታ ፈልግልኝ ብዬው ስለነበረ ሌላ ጊዜ ስልክ አስደውሎ “አዲስ አበባ ቦታ ተገኝቶልሃልና አሁን ና” ብሎ መልእክት ላከብኝ ፡፡ መልእክቱ በደረሰኝ ጊዜ ለመሄድ ብነሳም ምንም መጓጓዣ  አልነበረኝም ያው እንደሚታወቀው ለምነን የተገኘውን  ከተማሪ ጋር ነው ተካፍለን የምንበላው እንጂ ምንም ጥሪት የለንም፡፡ የተማርኩባቸውን መጻሕፍት ሸጬ ሁለት ተማሪዎች አስከትዬ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ፡፡ አዲስ አበባ ስደርስ የትምህርት ቤት ጓደኛዬ መምህር ሰሎሞን ተቀብሎ  ከብፁዕ አቡነ ገሪማ ጋር አገናኘኝ፡፡ ብፁዕነታቸው  ያኔ የጅማና የኢሊባቡር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ነበሩ፡፡ ብዙ ጥያቄዎችን ከጠየቁኝ በኋላ ”መቱ ከተማ የካህናት ማሰልጠኛ አለ በዚያ ለካህናቱ ቅኔ እንድታስተምር ነው የጠራሁህ፡፡ ቅኔ፣ አቋቋም ፣ዝማሬ መዋሥዕት ፣ዜማ ትችላለህ?” ብለው ጠየቁኝ፡፡ ”አዎን እችላለሁ” አልኩአቸው፡፡

እንግዲህ በብፁዕነታቸው መልካም ፈቃድ ወደ ኢሊባቡር እንድሄድ ሆነ ወዲያውኑ ከቤተ ክህነት ደብዳቤ ተጻፈልኝ ሁለት ተማሪዎችን ይዤ ወደ ጅማ ከዚያ ወደ ኢሉባቡር ሄድኩ፡፡ ከ፲፱፻፹፫ እስከ ፲፱፻፹፮ ዓመተ ምሕረት ድረስ የተቀጠርኩበት መደቤ በቅኔ መምህርነት ስለነበር ቅኔ እያስማርኩ ቆይቻለሁ፡፡ ማሠልጠኛው በዓመት ፻ ካህናት ያሠለጥናል፡፡ ስልጠናው በዓመት ሁለት ጊዜ የሚካሄድ ነው በመጀመሪያው ዙር ከመስከረም እስከ የካቲት ፶ ካህን እናሠለጥናለን፤ በሁለተኛው ዙር ከየካቲት እስከ ሰኔ ፶ ካህናት እናሰለጥናለን፡፡ በዚህ ረገድ ከሥልጠናው ጋር ተያይዞ የእኛን ማሠልጠኛ ጨምሮ ሌሎች መሰል የካህናት ማሠልጠኛዎች በአኃት አብያተ ክርስቲያናት ይረዱ ነበር፡፡ ከዚያ የሚመጣው ገንዘብ ነው የማሠልጠኛው በጀት፡፡ ለምሳሌ የጎንደርና የጎጃም ካህናት የሚሠለጥኑት ባሕር ዳር ፤ የወሎ እና የትግራይ ካህናት መቀሌ፤ ምስራቅ ሸዋና

ሐረር ዝዋይ፤ እንዲሁም የወለጋ፣ የጅማ የኢሊባቡር ካህናት ደግሞ እኔ ከነበርኩበት መቱ ማሰልጠኛ ነበር የሚሠለጥኑት። ጥሩ ትምህርት ተሰጠ የምለው ያን ዘመን ነው።

በዚያ ብዙ ዓይነት የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ይሰጥ ነበር። እኔ ቅኔ ሳስተምር ሁሉም መምህራን አሉ የሐዲስ ኪዳን መምህር፣ የብሉይ ኪዳን መምህር፣ የአቋቋም መምህር፣ የቅዳሴ መምህር፣ የዜማ መምህር ይገኛሉ። ሁሉም የየራሳቸውን ክፍል ቢያስተምሩም ሌላው ሲያስተምር ደግሞ ቁጭ ብለው ይማራሉ። ሁሉም ሰው መምህርም ተማሪም ነው። ሁሉንም በማዋሐድ የወንጌል ትምህርት በደንብ የተሰጠበት ትምህርት ጊዜ ነበር። ትምህርቱ የሚሰጠው ለሚሠለጥኑት ካህናት ብቻ አይደለም በአካባቢ ለነበሩት ምእመናን እና የምእመናን ልጆች ሁሉ ነበር። ዘመኑ መናፍቅ የጠፋበት ዘመን ነበረ። ተሳትፎው በጣም ጥሩ የነበረበት ጊዜ ነበር። እነዚህ አሁን የቆጠርኳቸው ማሠልጠኛዎች የቤተ ክርስቲያኒቱ አንደበቶች ነበሩ። ዛሬ እነርሱ ቢኖሩ ኖሮ ቤተ ክርስቲያን ባልተቃጠለችም ነበር መናፍቃንም ባልበዙ ነበር።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ማሠልጠኛዎቹ መቀጠል አልቻሉም ነበር? ምን ነበር ምክንያቱ?

***መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ ፦*** ከተወሰነ ዓመታት በኋላ ከአራት አብያተ ክርስቲያናት ለማሠልጠኛዎቹ የሚመጣው በጀት ቆመ ተባለ። ምክንያቱን ስንጠይቅ ርእሰ መምህሩ ሰብስበውን በጀቱን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ወደ ቅድስት ሥላሴ ኮሌጅ ማዞራቸውን ነገሩን። ለምሳሌ እኔ ከማሠልጠኛው የማገኘው ገንዘብ ፲፱ ብር ነበረ ቤተ ክርስቲያን መዘሙር ስለምቆም ፱ ብር አገኝ ነበረ አንድ ላይ ፳፰ ብርማለት ነው። ደሞዙ ትንሽ ቢሆንም ምግብ እዚያው ስለሚሠራ የምንመገበው ከማሠልጠኛው ነበረ ደቀ መዛሙርቱም ከዚያ ይመገቡ ነበረ። በጊዜው በጀቱ ወደ ቅድስት ሥላሴ እስኪዞር ድረስ ሁሉ ነገር የተመቻቸ ነበረ። ከዚያ በኋላ ግን ድርጅቱ ሲዞር መምህራን እና ተማሪዎች እንዲበተኑ ምክንያት ሆነ።

በጊዜው እንደ ዝዋይ ሐመረ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ገዳም የነበሩ የካህናት ማሠልጠኛዎች ራሳቸውን የቻሉ ቀደም ሥራ ሰርተው የነበሩ በራሳቸው ገንዘብ ለመቀጠል በቅተዋል። እንደነ መቱ የካህናት ማሠልጠኛ እኔ የነበርኩበት ማለት ነው እና ሌሎች ማሠልጠኛዎች ደግሞ አቅም ስላልነበራቸው መምህራንን ደቀ መዛሙርትንም ለማሰናበት ተገደዋል። "የምንከፍላችሁ ደሞዝ የለም ወደ የመጣችሁበት ወደ ሀገራችሁ ሂዱ" ብለው አሰናበቱን። ሁሉም መምህር ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ እኔም ወደ አዲስ አበባ መጣሁ። አዲስ አበባ መጥተን የምናስተምርበት ማሰልጠኛ ጠይቀን ነበር አዲስ አበባ ላይ ማሠልጠኛ ሳይሆን ደብር ነው የምንሰጣችሁ የሚል መልስ ተሰጠን ሆኖም ቦታውን ሳናገኝ እስከ ስድስት ወር ቆየን።

በዚህ መሃል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት መንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ማርያም አስቀድሰው ሲወጡ ሦስት ቀን በተከታታይ አገኙኝ በሦስተኛው ቀን ግን ቆም ብለው "ይህ ሰውዬ ችግሩ ምንድነው" ብለው ጠየቁ ሊቂ ብርሃኑ መኮንን ችግሬን እና ያለሥራ መቆየቴን ያውቁ ስለነበር "የቅኔ መምህር ነው ቦታ ይሰጠው ሌላ ቸግር የለበትም " ብለው አስረዱልኝ በዚህ ጊዜ ብፁዕነታቸው "እኛ እንፈልገዋለን እዚህ ቅደስት ማርያም ቶሎ ይጻፍለት" ብለው ፈቀዱልኝ።ይህን ሲሉኝ ደስታዬ ወደር አልነበረውም።

***ስምዐ ጽድቅ፦*** ስለዚህ መንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ማርያም ሥራውን ጀመሩ ማለት ነው?

***መጋቤ ምሥጢር መምህር አፈ ወርቅ፦*** አልጀመርኩም ቅዱስነታቸው እንዳዘዙ ለጊዜው ይጻፍልሃል ተብዬ ነበር በማግሥቱ ወደ ሊቂ ብርሃኑ ስሄድ ግን የብፁዕነታቸው ቃል ተፈጻሚ አልሆነም "እኔ ለቅድስት ማርያም አልጽፍልህም ሂድ ወደ ሀገረ ስብከቱ ብፁዕ አቡነ ማትያስ እዚያ ይጠብቁሀል" አሉኝ። አሁን ካናዳ የሚገኙት ብፁዕ አቡነ ማትያስ በወቅቱ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ነበሩ። በነገሩኝ መሠረት ወደ ብፁዕ አቡነ ማትያስ ሄድኩኝ። እሳቸውም ገና እንዳዩኝ "ለምንድነው ፓትርያርክ ሲመጣ አላስገባ አላስወጣ እያልክ የምትጮኽ?" አሉኝ ። እኔም "አባታችን ምን ላድርግ ራበኝ መልአክ አይደለሁ ሰው ነኝ ምን ልብላ? የት ልደር? ይገዬ የመጣሁትን ገንዘብም ጨርሻለሁ እና ቸግሮኝ ነው" አልኳቸው። "ምነው ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ እንዲሁም አስኮ

ገብርኤል፣ ምልክት አድርጌልህ ነበር ለምን አልገባህም?'' አሉኝ ። እኔም "ይኸው ርእሰ መምህሩን ይጠይቋቸው ሁለቱም ቦታ አልጽፍም ብለው አስቀርተዋል'' አልኳቸው። ብፁዕነታቸው ካሳሁን የሚባሉትን (ያን ጊዜ የሀገረ ስብከቱ ርዕሰ መምህር) ጠርተው ሲጠይቁ ገነተ ጽጌ በራሳቸው ሰው ስላመጡ ሌላ ተጨማሪ አንፈልግም ብለው ነው፣ እስኮ ገብርኤልም በጆቱ ተመልሷል ስላሉ ልጽፍላቸው አልቻልኩም አሉ። አቡነ ማትያስም " ቅዱስ ፓትርያርኩ እንዲቀጠሩ ስላዘዙ ነገ ባስቸኳይ እንዲጽፉላቸው ብለው ተቆጡ። ርእሰ መምህሩም ጽፍልሃለሁ ከነገ ወዲያ ና ብለው አዘዙኝ። በተባልኩት ቀን ሄድኩ። በሥራ አስኪያጁ በሊቀ ካህናት አለማየሁ ኀይለ ሥላሴ የተፈረመ ፸፭ ብር እያገኙ ደብረ ሲና ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን እንዲያገለግሉ የሚል ደብዳቤ ደረሰኝ። አዲሱ ገበያ ያለው ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው።

ደብዳቤው እንደደረሰኝ ወዲያው ወደ ደብረ ሲና እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ሄድኩ። ደሞዙ ብዙም ባይሆን ቦታው ጥሩ ቦታ ነበረ፤ እኔም ደስተኛ ነበርኩ። እዚያ አለቃ ኤልያስ የሚባሉ ታላቅ ሰው ነበሩ በወቅቱ ከአለቃ አያሌው ታምሩ ጋር በጠቅላይ ቤተ ክህነት የጉባኤ ሊቃውንት ዋናዎች ነበሩ። አለቃ ኤልያስ እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን እሑድ እሑድ ወንጌል የሚያስተምሩት እርሳቸው ነበሩ። በጊዜው የማታ ስብከተ ወንጌል አይሰጥም ነበርና የደብሩ ሰበካ ጉባኤ ተነጋግሮ ደብዳቤ በመጻፍ እንድጀምር ኃላፊነቱን ለኔ ሰጡኝ። እኔም ከካህናት ማሰልጠኛ ከኮርስ ስለሄድኩ የደብሩ የአቋቋም መምህር ከሆነው መምህር ዳንኤል ጋር እየተፈራረቅን ለመጀመሪያ ጊዜ የማታ ስብከተ ወንጌል ጀመርን።

በጊዜው ብዙ ሕዝብ እየመጣ መማር ጀመረ። የአካባቢው ሕዝብ ወንጌል የተጠማ ሕዝብ ነበርና እየበዛ ሄደ። በኋላ ላይ አለቃ ኤልያስ "እንደግዲህ እኔ ደክሞኛል በኔ ቦታ እየገባህ አስተምር ብለው'' ሁሉንም ወደ እኔ አስተላለፉ። ሕዝቡም ተቀበለው በየተራ እየገቡ የመድኃኔ ዓለም ዝክር፣ የእግዚአብሔር አብ ዝክር ይዘክሩ ነበር እኔም በየወሩ እየገባሁ አስተምራለሁ። የእግዚአብሔር አብ ሕዝብ እንደ ከተማ ሕዝብ ሰምቶ ሂያጅ አይደለም ትምህርት ተቀባይ ጠንካራ መንፈሳዊ፣ ቅዱስ ሕዝብ ነው። ከስብከተ ወንጌሉ በኋላም ማታ ማታ የቅኔ ትምህርት ነበር በተለይ ከጎጃም እና ከጎንደር የሚመጣው ወደ ከተማ መግቢያው በሩ በዚያ ስለሆነ ብዙ ተማሪዎች ወደ እኛ እየመጡ ያርፉ፣ይማሩም ነበረ። ብዙዎች ቅኔ ተቀኝተዋል፣ ትልቅ ደረጃም ደርሰዋል። እንግዲህ እዚያ ብዙ ጊዜዬን ያሳለፍኩት በስብከተ ወንጌል እና ቅኔን በማስተማር ነው።

ከዚያ በኋላ ግን አገልግሎት እጅግ አስቸጋሪ ሆኖብኝ ነበር። አንዴ ሌቦች የጽሕፈት ቤቱን ጣሪያ ቀደው ገብተው ገንዘብ ሰረቁ። የቤተ ክርስቲያኒቱ የጥበቃ ሠራተኞች ሰበካ ጉባኤ ላይ ተጠርተው ሲጠየቁ መምህር አፈወርቅ ጋር የሚመጡ፣ መቃብር ቤት የሚያድሩ ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡ ብዙ ተማሪዎች ስላሉ ግቢውን መቆጣጠር አልቻልንም አሉ። መቃብር ቤት ያሉት ይልቀቁልን የሚል አቤቱታም በጽሑፍ ለጽሕፈት ቤቱ አስገቡ። ሰበካ ጉባኤውም ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም መቃብር ቤቱን ለቅቄ እንድወጣና አንድም የአብነት ተማሪ እንዳይገኝ የሚል ደብዳቤ ጻፈልኝ። እውነት ለመናገር እጅግ ያዘንኩበት ጊዜ ቢኖር ያኔ ነው ምክንያቱም እኔም ኾንኩ የማስተምራቸው በርካታ የአብነት ተማሪዎች ሊበተኑ መሆኑ ነው ያሳዘነኝ። በመሠረቱ ቦታው ከ፲፱፻፹፯ ዓመተ ምሕረት ጀምሮ ያገለገልኩበት ቦታ ነው። ከዚያ በፊት ከዚያ ቦታ ስለመሄድ አስቤ አላውቅም ነበር። አንዴ አስታውሳለሁ ጓደዬ ደብረ ገሊላ ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ሊያስቀጥረኝ ወስኖ ነበር በጊዜው ግን "አባቴ አለቃ ኤልያስ ከቦታው እንዳልሄድ ቃል አስገብተውኛልና አልሄድም'' ጥሪውን አልቀበልም ብየው ነበር። አሁን ግን በደብዳቤ ጭምር መቃብር ቤቱን ለቅቄ እንደወጣ ስለታዘዝኩኝ ወደ ሌላ ቦታ እሄድ ዘንድ እግዚአብሔር አምላክን "ደሞዝ አልልም ሰው ካለበት ብቻ አድርሰኝ'' እያልኩ በጸሎት እማጸነው ነበር።

*ይቀጥላል...*

# “ወራሪ እየተባልን ከመገደልና ከመሰደድ ወጥተን የሀገር ባለቤትነታችንን ልናረጋግጥ ይገባል”

***አቶ ፋንታሁን ዋቄ***

***በማኅበረ ቅዱሳን የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ)***

**በካሣሁን ለምለሙ**



**አቶ ፋንታሁን ዋቄ**
**በማኅበረ ቅዱሳን የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ**

## ክፍል አንድ

በኢትዮጵያ ባለፉት ሠላሳ ዓመታት ውስጥ ኦርቶዶክሳዊያን ክርስቲያኖች ለአሰቃቂ ግድያና ስደት ተዳርገዋል፡፡ በተለይም የመንግሥትን ለውጥ ተከትሎና የፓለቲካ ትርክት ታክሎበት ክርስቲያኖች በየጊዜው የችግሮች ሁሉ ሰለባ ሆነዋል፡፡ ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ በክርስቲያኖች ላይ የደረሰው ግፍ ግን እስካሁን ከደረሰው ግፍ ሁሉ በዓይነቱም ሆነ በመጠኑ የተለየና እጅግ አሰቃቂ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም፡፡ ሐምሌ 28 ቀን 2010 ዓ/ም በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከተፈጸመው ጥቃት አንስቶ በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል አንዳንድ አካባቢዎችና በደቡብ ክልል በክርስቲያኖች ላይ የተፈጸሙ ጥቃቶች እጅግ ጭካኔ የተሞላባቸው ናቸው፡፡

ክርስቲያኖች በኦርቶዶክሳዊነታቸው ብቻ በተለያየ ጊዜያት በአሰቃቂ ሁኔታ በገጀራ ተቀልተው፣ በቆንጨራ ተቆራረጠው፣ በጦር ተወግተው፣ በጩቤ ተዘክዝከው፣ በሜንጫ ተተልትለው፣በዱላ ተቀጥቅጠው እንዲሁም በድንጊያ ተወግረው ሞተዋል፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው ሕገ አራዊት ባለበት ሀገር ሳሆን ሰዋዊ ሕግ ባለበት ሀገር ነው፡፡ ክርስቲያኖች በየአካባቢው በሕይዎት የመኖር ተፈጠሮዊ መብታቸው ተነፍጎ በሚከተሉት እምነት ብቻ ተለይተው መገደላቸው ለምን ይሆን? ስንል እንጠቃለን፡፡ የተከበራችሁ አንባቢያን “ለምን ይሆን” ስንል ለጠየቅነው ጥያቄ ምላሽ እንዲሰጡን በማኅበረ ቅዱሳን ዋናው ማእከል የትብብርና የሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ማስተባበሪያ ክፍል ኃላፊ የሆኑትን አቶ ፋንታሁን ዋቄን ለቃለ መጠይቅ ጋብዘናችዋል፡፡ ከእርሳቸው ጋር ያደረግነውን ቆይታም እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** በኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ላይ የሚፈጸሙ ሁለንተናዊ ጥቃቶች የጀመረው መቼ ነው?

***አቶ ፋንታሁን ዋቄ፡-*** የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንዋን ማጥቃት የተጀመረው ከቅርብ

ዓመታት ወዲህ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለረጅም ዘመናት ይፋዊ ጥቃት የተከፈተባት ቢሆንም ያንን ሁሉ በደል በጥበብ ተሻግራ እየኖረች ያለች ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ የመጀመሪያውን የቤተ ክርስቲያን ጥቃት የፈጸመችው ዮዲት ጉዲት ስትሆን ሁለተኛው ደግሞ በኦቶማን ቱርክ ቀለብ ይሰፈርለት የነበረው የአዳሉ ግራኝ አሕመድ ያደረሰው መጠነ ሰፊ ጥቃት ነው፡፡

ይህ ግለሰብ (ግራኝ አሕመድ) በወቅቱ ኢትዮጵያን አፍርሶ የኢትዮጵያን አንጡራ ሀብት ወደ ቱርክ ያግዝ የነበረ ፀረ ኢትዮጵያ ነበረ፡፡ ፀረ ቤተ ክርስቲያን በመሆኑም በቤተ ክርስቲያን ላይ በፈጸመው ጥቃት ዘመን የማይሽረው ጠባሳ ጥሎ አልፏል፡፡ ከግራኝ አሕመድ ጥፋት በኋላ ደግሞ ጣሊያኖችና ፓርቹጋሎች ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን ከፋፍለው የካቶሊክ እምነት ተከታይ ለማድረግ ባደረጉት ጥረት በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ታሪክ የማይዘነጋው ግፍ ተፈጽሟል፡፡ ፋሽስት ጣሊያኖች ሁለት ጊዜ ሀገራችንን ሲወሩ የኢትዮጵያ የአንድነትና የማንነት ምስጢራዊ ቋጠሮ የሆነችውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት ዘመናዊ መሣሪያን ከመጠቀም በተጨማሪ በምእመናን ላይ የመርዝ ጋዝን ተጠቅመዋል፡፡ በነዚህ የግፍ ዘመናት ሁሉ ባንዳ ሙስሊሞችና ሌሎች ከጠላት ጋር አጋርነት ፈጥረው ቤተ ክርስቲያን ሲያጠቁና ሲያስጠቁ ነበር፡፡

ከአርባ ዓመታት ወዲህ ‹‹የብሔር ነፃ አውጭ ነን›› የሚሉ የፖለቲካ ኃይሎች ቤተ ክርስቲያንን በጠላትነት በመፈረጅና በርዕዮተ አለማቸው ጭምር በማካተት ማታገያ ሲያደርጓት ቆይተዋል፡፡ የትግራይ ነፃ አውጭ ግንባር የተባለው የፓለቲካ ድርጅት "የኦርቶዶክስን አከርካሪ መስበር" የሚል ርዕዮተ አለም ይከተል እንደነበረ ያዘጋጀው ሰነድ ምስክር ይሆናል፡፡ በዚሁ ፓለቲካ ድርጅት በከፍተኛ አመራርነት ይሠሩ የነበሩት ዶ/ር አረጋዊ በርሄ የተባሉ ግለሰብ ሳይቀር በመጻሕፋቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን "አከርካሪ መስበር" የፓለቲካ ድል እንደሚያስገኝ ገልጠዋል፡፡ "የኦሮሞ ሕዝብ ነፃ አውጪ ነኝ" ብሎ የተነሳው የፓለቲካ ቡድን ደግሞ ‹‹ቤተ ክርስቲያን የወራሪዎች ፊት አውራሪ ነች›› ብሎ ተነሳ፡፡ በዚህ ምክንያት ኦሮምያ ክልል ተብሎ በተከለለው የሀገሪቱ ክፍል በሚኖሩ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ላይ ይፋዊ በደል መፈጸም ጀመረ፡፡ "የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያለችው በሰሜኑ ሀገራችን ክፍል ነው እንጂ እኛጋ ያለችው ባህላችንና መሬታችንን የወረረችው ነች" የሚል የሀሰት ክስም ያቀርባሉ፡፡ በክልሉ ያደጉ ሕፃናትም ይህንን መሰል የጥፋት መርዝ ሲጋቱ በመኖራቸው ካደጉ በኋላ በዚህ ወቅት በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ እያየን ያለነውን ጥፋት ያለምንም ርህራሄ እየፈጸሙ ይገኛሉ፡፡

አንደንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን የሚመሯት ሌላ አካላት ናቸው ብለው ስለሚያስቡ "ከጭቆና ለመውጣት ቤተ ክርስቲያንን ማጥፋት ነው" የሚል ትርክት በትውልዱ አእምሮ ውስጥ ስለገባ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ የጥቃት ኢላማ ትሆናለች፡፡

"የኦሮሞን ሕዝብ ከጭቆና ነፃ አወጣለሁ" የሚል "የኦሮሞ ምሁር ነኝ" ባይ ሕዝብን ከጭቆና ለማውጣት ቤተ ክርስቲያን እንደጨቋኝ በመቁጠር ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያልተገባ ግብግብ ውስጥ ይገባል፡፡ እነዚህ ኃይሎች ብቻ ሳይሆኑ ኮሚኒስታዊ አስተሳሰብ ያላቸው ኃይላት በሙሉ ሆን ብለው ቤተ ክርስቲያንን ለማጥቃት ይረባረባሉ፡፡ የቀኝ ገዥዎቻቸውን ኮሚኒስታዊ አስተሳሰብ እውን ለማድረግ በዳይ ያልሆነችን ቤተ ክርስቲያን ያልሆነ ሥም በመስጠት ዛሬም ትናንትም ሁለንተናዊ ጥቃት እያደረሱባት ይገኛሉ፡፡

የቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ ጥቃት ባለፉት ሦስት ዓመታት ብቻ የተፈጸመ ሳይሆን ከበደኖ እስከ በሻሻ፣ ከሊሙ ገነት እስከ ዶዶላ፣ ከኮፈሌ እስከ ሻሸመኔ እንዲሁም ከካራሚሌ እስከ ጅግጅጋ ድረስ በጥናት የተደገፉ ኦርቶዶክሳውያንን የማጥፋት ግፍ ሲፈጸም ነበር፡፡ በነዚህ ቦታዎች ሁሉ የተፈጸሙ ኦርቶዶክሳውያንን የማጥፋት ተግባራት ሁሉ ከላይ በተገለጠው አስተሳሰብ ምክንያት የተፈጸሙ የግፍ ወንጀሎች ናቸው፡፡ በቅርቡ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አንዳንድ አካባቢዎች በኦርቶዶክሳውያን ላይ የተፈጸመው የዘር ማጥፋት ተግባር ርዕዮተ አለማዊ አመራር ያለው ነው፡፡ በክልሉ የደረሰውን ጥፋት ወደ

ግጭት ዝቅ አድርጎ የሚመለከት አካልም ጥፋቱን ደብቆ ሆን ብሎ ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ያለመ ፀረ ኦርቶዶክስ ነው:: በዚህ ዓመት በተከታታይ የተከሰተው ኦርቶዶክሳውያንን የማጥፋት ተግባር የታቀደ፣ ፍልስፍና ያለው እንዲሁም ኦርቶዶክስን ሀገር አልባ የማድረግ ዓላማ ያለው ነው::

> አንደንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን የሚመሯት ሌላ አካላት ናቸው ብለው ስለሚያስቡ "ከጭቆና ለመውጣት ቤተ ክርስቲያንን ማጥፋት ነው" የሚል ትርክት በትውልዱ አእምሮ ውስጥ ስለገባ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ የጥቃት ኢላማ ትሆናለች::

***ስምዐ ጽድቅ፦*** በኦሮሚያ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች በምእመናንና በንብረታቸው ላይ የተፈጸመውን ጥቃት አስመልክቶ ቤተ ክርስቲያን መግለጫ እንዳወጣች ይታወሳል:: ይህንን መግለጫ እርስዎ እንዴት ገመገሙት?

***አቶ ፋንታሁን ዋቄ፦*** ቤተ ክርስቲያን በኦሮሚያ ክልል የተፈጸመውን ጥቃት አስመልክቶ ያወጣችው መግለጫ በክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው ጥቃት መንግሥታዊ መዋቅርን የተላበሰ፣ በርዕዮተ ዓለም የታገዘ እንዲሁም በፍልስፍና የታጀበ ጥቃት መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ በግልጽ ያወጀችበት ነው:: ቤተ ክርስቲያን ያወጣችው መግለጫ ማስመሰል የለሌበትና በአደባባይ ወጥታ ለተከታዮቿ መሬት ላይ ያለውን እውነት ያስረዳችበት ነው:: እንደምናስታውሰው ከዚህ ቀደም ይሰጡ የነበሩ መግለጫዎች አብዛኛውን ጊዜ እውነቱን ከመግለጽ ይልቅ መንግሥትን ወደ መማጸን ያደሉ ነበሩ:: በዚህ ጊዜ የወጣው መግለጫ ግን ጠንካራና እውነቱን ያወጣ ሆኖ አግኝቸዋለሁ::

ቤተ ክርስቲያንን እያጠቃ ያለው ጥቂት የስርዓቱ ደጋፊዎች ሳይሆኑ ራሱ መንግሥታዊ ሥርዓቱ እንደሆነ በግልጽ ያስቀመጠችበት መግለጫም ነው:: ቤተ ክርስቲያንን የመንግሥት ኃይል እያጠቃት እንደሆነ የሚያመለክተው በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች በተፈጸሙ አንዳንድ ጥቃቶች የመንግስት ኃላፊዎችና የፖሊስ አዛዦች ሳይቀር የጥፋቱ ተባባሪዎች መሆናቸው ነው:: በአንጻሩ እራሳቸውን በሚከላከሉ ክርስቲያኖች አጥቂዎች ጉዳት ሲደርስባቸው አምቡላንስ ሲላክላቸው ተጠቂዎች ደግሞ በእሳት ተቃጥለው እንዲሞቱ ይደረጋል:: ከሞት የተረፉ ምእመናን ደግሞ የደረሰባቸውን በደልና መከራ እንዳይናገሩ እና ሰብአዊ ድጋፍም እንዳይደረግላቸው የየአካባቢው ባለሥልጣን መከልከላቸውንም መግለጫው በሚገባ አሳይቷል::

አባቶቻችንም ይህንን በይፋ መናገር ይጠበቅባቸዋል:: ምእመናን የመግለጫው ሐሳቡ በደንብ እንዲገባቸው የመተንተንና የማብራራት ሥራ ኦርቶዶክሳዊ ሚዲያዎችና የሃይማኖት አባቶች ይጠበቅባቸዋል:: ምእመናንን በማስተባበር ራሳቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን ነቅተው እንዲጠበቁ የሚያደረግ ምክረ ሀሳብ አባቶቻችን ማቅረብ አለባቸው:: መንግሥት የኦርቶዶክስ ጠላት እንዲሆን ማድርግ ሳይሆን ኦርቶዶክስ የመንግሥት እንድትሆን የማድረግ ሥራ መሠራት አለበት:: ምእመናን በትኩረት እንዲሰሩ የማስተባበርና የማንቃት ኃላፊነት ያለው ከአባቶች ትከሻ ላይ ነው:: ስለሆነም አባቶች ሳይፈሩና ሳያስመስሉ እውነታውን መጋፈጥ አለባቸው:: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ መሠረተ ዘረኝነት ቦታ ሥለሌለው በአባቶች መካከል በዘረኝነት የተለከፉ ካሉ በጥንቃቄ ወደ እውነተኛው መሥመር በመመለስ በጋራ የቤተ ክርስቲያንን ልዕልና መጠበቅ ያስፈልጋል:: አባቶቻችን ዘረኝነትን የሚጸየፍ ትውልድ መፍጠርና የልጆቻቸውን አንድነት መጠበቅ አለባቸው::

# ልጆች ዘወትር ጸልዩ!

በእንድርያስ ስንታየሁ

እንደምን ሰነበታችሁ ልጆች? እግዚአብሔር ይመስገን አላችሁ? መልካም፤ እግዚአብሔር አምላካችን የተመሰገነ ይሁን።

ልጆች የዛሬ ትምህርታችን ስለጸሎት ነው፤ በመጀመሪያም የቃሉን ትርጉም እንመልከት።

ጸሎት ‹‹ጸለየ›› ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ነው። የቃሉ ፍችም ለመነ፣ተማጸነ ማለት ሲሆን ጸሎት ማለት ልመና ወይንም መማጸን ማለት ነው፤ ጸሎት የሚቀርበው ለእግዚአብሔር ወይም ወደ እግዚአብሔር ነው።

ጸሎት ብዙ ጥቅሞች አሉት። ከብዙዎቹም ውስጥ ጥቂቶቹን እንደሚከተለው እንመለከታለን።

1. እግዚአብሔርን ለማመስገን ይጠቅመናል፤
2. በጸሎት በደላችንን እና ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር እንናዘዛለን (እንናገራለን) ይቅርታውንም እንለምናለን፤
3. ከእግዚአብሔር ዘንድ የፈለግነውንና የጎደለንን ለማግኘትም ያስችለናል፤
4. የእመቤታችንን እና የቅዱሳንን አማላጅነት ለመለመን እንጸልያለን
5. መንፈሳዊ ኃይል እንድናገኝ ያስችለናል።

እንግዲህ ጸሎት ይህን ያህል ጥቅም እንዳሉት ከተረዳን አቡነ ዘበሰማያት (አባታችን ሆይ) በግእዝና በአማርኛ እንጸልያለን።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

## አቡነ ዘበሰማያት በግእዝ

፩. አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ፤ ትምጻእ መንግሥትከ። ወይኩን ፈቃድከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር
፪. ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ ሀበነ ዮም
፫. ኅድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ከመ ንህነኒ ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ፤
፬. ኢታብኣነ እግዚኦ ውስተ መንሱት። አላ አድኅነነ፥ ወባልሓነ እምኵሉ እኩይ
፭.እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት ኃይል፥ ወስብሐት፤ ለዓለመ ዓለም።

## በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ

፩. በሰላመ ገብርኤል መልአክ ኦ እግዝእትየ ማርያም ሰላም ለኪ ድንግል በሕሊናኪ፣ ወድንግል በሥጋኪ

፪. እመ እግዚአብሔር ጸባዖት ሰላም ለኪ

፫. ብሩክት አንቲ እምአንስት ወብሩክ፤ ፍሬ ከርሥኪ፤

፬. ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ

፭. ሰአሊ ወጸልዩ ምሕረተ ኀበ ፍቁር ወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ይሥረይ ለነ ኃጣውኢነ።

## አባታችን ሆይ በአማርኛ

1. አባታችን ሆይ፥ በሰማይ የምትኖር፥ ስምህ ይቀደስ፥ መንግሥትህ ትምጣ፥ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነ፣ እንዲሁም በምድር ይሁን፣
2. የዕለት እንጀራችንን ስጠን ለዛሬ፥
3. በደላችንን ይቅር በለን፥ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል፥
4. አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን፥ ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ፥
5. መንግሥት ያንተ ናትና፣ ኃይል፥ ክብር፥ ምስጋና ለዘለዓለሙ አሜን!

## በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ

1. እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ፥ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን። በሐሳብሽ ድንግል ነሽ፥ በሥጋሽም ድንግል ነሽ።
2. የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ሆይ ሰላምታ ላንቺ ይገባሻል።
3. ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ፥ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።
4. ጸጋን የተመላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ፣ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና።
5. ከተወደደው ልጅሽ ከጌታንችን መድኃታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታን ለምኝልን፤ ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ ለዘለዓለሙ አሜን!

ልጆች! እስከ ዛሬ ጸሎት ያልጀመራችሁ ካላችሁ ዛሬውኑ ጀምራችሁ ዘወትር ጥዋት ከእንቅልፋችሁ ስትነሡ፣ ምግብ ከመመገባችሁ በፊትና ተመግባችሁ ስትጨርሱ እንዲሁም ከመኝታ በፊት ጸሎት አድርጉ። ጸሎት የጀመራችሁ ሕፃናት ደግሞ ሳታቋርጡ ዘወትር ጸልዩ! ይህንን ስታደርጉ አምላካችን እግዚአብሔር ይወዳችኋል፤ ከበሽታም ሁሉ ይጠብቃችኋል እሺ!

በመጨረሻም በቤተ ክርስቲያን ስትጸልዩ እንዴት መጸለይ እንዳለባችሁ በሚቀጥለው ትምህርታችን እናቀርብላችኋለን፤ እስኪዚያው መልካሙንና የተወደደውን ነገር ሁሉ እንመኝላችኋለን፤ ደኅና ሰንብቱ!

# "ቅርሶችን መጠበቅ ማንነትን መጠበቅ ነው"

**በረቂቅ መቻል**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከስድሳ ሚሊዮን በላይ አማኝ ያላት፣ በውስጧ ብዙ ሃይማኖታዊና ሀገራዊ ቅርሶችን ይዛ በሀገር በቀል ዕውቀቶቿም ለኢትዮጵያ የሥልጣኔ አሻራዋ መሆኗ እሙን ነው:: ታዲያ ለእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ቅርስና ልዕልና መነሻ በመሆን ትልቁን አስተዋጽኦ ያበረከተችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን::

ይሁን እንጂ አሁን ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶቿ ለሀገር ያበረከቱትን አበርክቶት በዘመን ከፍታ ላይ ቆመው እንዳይመለከቱ ልባቸው የጠፋ፣ ዐይናቸው የተንሸዋረረ ግለሰቦችም ሆኑ ጽንፈኛ ቡድኖች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበዙ መምጣታቸው አሳዛኝ ነው::

ከቅርብ ዓመታት ወዲህም እየመጣ ካለው ትውልድ ውስጥ አንዳንድ ግለሰቦች የሀገራችንንም ሆነ የሃይማኖታችንን ታሪክና ቅርስ እንዲሁም የማንነት ገጽታውን ጥላሸት እየቀቡ ይገኛሉ:: ስለዚህነ ገን እንዴትና ማን ቅርሶቻችንን ለትውልድ ያሻግር? ሀገሬና ሃይማኖቴ ያፈሩትን የጋራ ታሪክና ቅርስ ማን ይሆን የሚጠብቀው ብዬ እንድታዘብ የተገደድኩባቸው ዐበይት ምክንያቶችም አሉኝ::

ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እና ኦርቶዶክስ ሃይማኖት በዓለም መድረክ እንደ አንድ ልብ መክረው በሰላም፣ በበጎነት፣ በመከባበር ለሌሎች አርአያ በመሆን የሚታወቁ፣ምእመናን በመፈቃቀር አብረው የሚኖሩ ነበሩ:: በዚህም ምክንያት ባህላቸውን፣ ዕሤታቸውን፣ ቅርሶቻቸውን ለመጠበቅ ችለዋል::

ይህ ብቻም አይደለም ቤተ ክርስቲያን የሀገር ባለውለታ የሆኑ የታላላቅ ነገሥታት ታሪክን ሰንዳ የያዘች ፣ ቅርሶችን በመጠበቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲመዘገብ ያደረገችበት የታሪክ ዐውድም ብዙ በመሆኑ የቀደሙት መንግሥታት በሚሄዱበት ሁሉ ከፍ አድርገዋት ቅርሶቿንና ልዕልናዋን አስጠብቀዋል::

አዲሱ የዘመን ብራናችን እንዲበላሽና ባለፉት ጥቂት ዓመታት ሃይማኖትን ለማጥፋት፣ ቅርሶቻችን ለትውልድ እንዳይቀመጡ በማድረግ አንዳንድ ግለሰቦችና አክራሪ ቡድኖች በሃይማኖታችን ላይ እያደረጉት ያለውን ዘመቻ እንዴት ተባብረን እናስቁም? የሚለውን እናስብ::

እነዚህን ቅርሶች እንዳይጠፉ በትጋት የሚጠብቁት ታላላቅ አባቶች ከየቦታው በግፍ ተገድለዋል፣ ደማቸውም እንደ አቤል ደም በሁላችን ሕሊና ውስጥ እየጮኸች ዓመቱ እንደዋዛ አልፏል:: በተለይ ስለ አብያተ ክርስቲያናት ሲሉ የንዋያተ ቅድሳት መቃጠል አስጨንቋቸው ሥጋቸውን የሚገድሏቸውን ሳይፈሩና ለሥጋቸው ሳይሳሱ የተቃጠሉ፣ ቤተ ክርስቲያናቸውን ከቃጠሎ ለመከላከል ሲሉ በሚሰጡት ተግሣጽ ዘወትር ግፍና መከራን በሰማዕትነት የተቀበሉትን ልንረሳቸው አንችልም::

በእርግጥ ቤተ ክርስቲያንን የናቋትና ሁሉ ነገ እውነቱ ሲገባቸው ከእግሯ ዝቅ ብለው ማሪን እንደሚሉ አምናለሁ:: ምክንያቱም በቅዱስ መጽሐፍ ትንቢት እንዲህ የሚል ተጽፏል "ለአንቺም የማይገዙ ነገሥታት ይሞታሉ፤ እነዛም አሕዛብ ፈጽመው ይጠፋሉ፤ የመቅደሴንም ስፍራ ያከብሩ ዘንድ የሊባኖስ ክብር፥ ጥዱና አስታው ባርስነቱም ወደ አንቺ ይመጣሉ የአስጨናቂዎችሽ ልጆች እየተንቀጠቀጡ ወደ አንቺ ይመጣሉ፤ የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ፤ የእስራኤል ከተማ ቅዱስ ተብለሽ ትጠሪያለሽ::" (ኢሳ. ፷፥፲፪-፲፬)

የትም ሊገኙ የማይችሉ ቅርሶችን የያዘች ቤተ ክርስቲያን በብርቅዬ ቅርሶቿ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ እንድትታወቅ ከማድረግ አኳያ የበኩሏን አስተዋጽኦ ማበርከቷ መዘንጋት አልነበረበትም::

አባቶቻችን ያቆዩልን ቅርስ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ሳስብ ይኸኛው ትውልድ ጥበብ መውረስ ይቅርና እንዳለ ጠብቆ ማቆየት አለመቻሉ ምን ያህል ተጠያቂ እንደሚያደርገው መገንዘብ ከባድ አይሆንም::

የዚህችን የታላቋን ቤተ ክርስቲያን ቅርሶችና ሀብቶች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ማንም እንደፈለገው ሲያደርጋቸው "መጣፉም ዝም ቁሱም ዝም" እንደሚባለው ዝምታው

እስከመቼ ነው? መጽሐፉ እንኳን የሚያነበው አለመኖሩ እንጂ አንዴ የተጻፈው ለዘላለም ይናገራል፡፡ በእውነቱ የቤተ ክርስቲያናችን ዜማ እንዲሁም መሣሪያዎቹ በሌሎች እየተወሰዱ ባንጻሩ ደግሞ የኛዎቹ መዝሙራት ከያሬዳዊ ዜማና መሣሪያዎቹ እየተፋቱ ዘፈን ዘፈን እየሸተቱ መሄዳቸው ዕለት ዕለት የምናይና የምንሰማው ቢሆንም ችግሩን ተረድቶ ሕጋዊ ማስተካከያ (ርምጃ) የሚወስድ አካል ከሌለ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የባለቤትነት መብታችንንም እንዳናጣ ያሰጋል፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያሏት የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች ማንነታቸው እንዳያጡ፣ ከሥሪታቸው እንዳይለዩ እና ጠፍተው እንዳይቀሩ ብሎም ተጠብቀው እንዲቆዩ የቤተ ክርስቲያን፣ አባቶች እና የቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናን በጋራ በመሆን ሊሠሩ ይገባል

በአጠቃላይ ቅርስን መጠበቅ ማንነትን መጠበቅ ነውና እነዚህ የማይነጣጠሉ ሀገርና ቤተ ክርስቲያንን በመጠበቅ እንዴት ለመጪው ትውልድ እናቆይ? ቅርስ ማጣት ታሪክ ማጥፋት ነውና የነገሥታቶቻችን ታሪክ፣የቤተ ክርስቲያን ቅርስ ሁሉም የኢትዮጵያ መሠረቶች በመሆናቸዉ ሐሳብና መፍትሔ ቢሆኑ ያልኳቸውን ጥቂት ሐሳቦች አክዬ የዛሬ ትዝብቴን እቋጫለሁ፡፡

ቅርሶች የአንድን ማኅበረሰብ ታሪክና ማንነት በማሳየት ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ ለቅርሶቹ ግንባታ የዋሉት ቁሳቁሶችና አሠራራቸው ለዘመናዊ ሥነ ሕንፃ መሣሪያም ነው፡፡ ቅርሶች ለሚገኙበት አካባቢ ነዋሪዎች ሥራ ከመፍጠር ጀምሮ ለሀገር ውስጥና የውጪ ኢንቨስትመንት መስፋፋትና ለቱሪዝም ዕድገት ያላቸው አስተዋጽኦም ታላቅ ነው፡፡ ስለዚህ ቅርሶች ለሀገርና ለቤተክርስቲያን ያላቸውን ጠቀሜታ ለምእመናን በየዐውደ ስብከቱ እንዲሁም በሥርዐተ ትምህርት ተካቶ በሕዝቡ ዘንድ ግንዛቤ እንዲጨምር ቢደረግ መልካም ነው፡፡

፩. የቤተ ክርስቲያንም ሆነ የሀገርን ቅርሶች የሚመለከታቸው አካላት በእኩል አይተው ተገቢውን እንክብካቤና ጥበቃ ቢያደርጉ፤

፪. የቤተክርስቲያን ቅርሶች የሀገር ቅርሶች እንደመሆናቸው መንግሥት ሁሉንም የኢትዮጵያ ቅርሶች እኩል ቢመለከት፣ ከርዳታ ሰጪዎች ከሚመጣው ገንዘብ ላይ በቤተ ክርስቲያን ለሚገኙ ቅርሶች በጀት ቢበጅትና ቅርሶቹ የሚገኙባቸው ነባራዊ ሁኔታ ተመዝነው በየጊዜው እድሳት ቢደረግላቸው፤

፫.የቤተ ክርስቲያን ቅርሶች የሀገሪቱ ዜጎች (ምእመን) ብቻ ሳይሆን የመላው ዓለም መገለጫ በመሆናቸው ለጥበቃቸው በጋራ መረባበረብ ቢቻል፤

፬. የቅርሶች ጥበቃ ጉዳይ በመንግሥት ወይም በበጎ አድራጊዎች ችሮታ ብቻ ግቡን ስለማይመታ የማኅበረሰቡን ተሳትፎ ማሳደግ፣ ማኅበረሰቡ ቅርሶችን እንዲጠብቅ ማበረታታት፤ ብሎም የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ማድረግ፡፡

፭. ቤተ ክርስቲያን በሁሉም ቅርሶቿ አሠራር እና አጠባበቅ ላይ ብቻ የሚሠራ በሊቃውንት አባቶቻችን የሚመራ በባለሙያዎች የተደራጀ አካል ቢኖራት፤ እያንዳንዱ ባለሙያ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ማእከላዊ በሆነ መንገድ ሥልጠና የሚያገኝበት ሁኔታ ቢቀረጽ እንዲሁም እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ቅርስ ሕጋዊ ጥበቃ ማግኘት የሚችልበት ሁኔታ ቢመቻች ቤተ ክርስቲያን ነገ ለልጆቿ የምታስረክበው ያልተበረዘ ቅርስ ይኖራታል፡፡

፮. የቅርሶቹ ባለቤቶች ውስጥ ከሆኑት አንዷ የሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፤ የሥነ ጽሑፍ ሀብቶቿ ይሰረቃሉ በሚል ስጋት ላለፉት ዓመታት ዲጂታላይዜሽንን እንደማታበረታታ ይነገራል፡፡ “በተለይም የውጪ ሀገር ምሁራን ዲጂታላይዝ ለማድረግ ሲመጡ፤ ቅርሶቹ ተዘረፉ ስለሚባል በቤተ ክርስቲያን ዘንድ የዲጂታይዜሽን ጥቅም ብዙም አይታይም፡፡ ደግሞም ቤተ ክርስቲያኗ በውጪ ተመራማሪዎች በቅርስ ጥናት ስም ከሚደርስባት የቅርስ ዘረፋ ቤተ ክህነት እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችም ለዲጂታላይዝ ተግባሩ ፈቃደኛ አለመሆናቸው ብዙም አያስደንቅም

ምክንያቱም ቅርሶች ይሰረቃሉ የሚለው የቤተ ክርስቲያን ስጋት መሠረት ስላለው ነው፡፡ ይሁንና ከዘመኑ ሥልጣኔ አንጻር ዛሬ ላይ ቅርሶችን ዲጂታላይዜሽን ማድረግ ደግሞ አማራጭ የሌለው ዘዴ ነው፡፡ ስለሆነም ዘመኑ ባፈራው ቴክኖሎጂ ቅርሶችን ሰንዶ መያዝ ተገቢ ነው እላለሁ፡፡

# ''በሃይማኖት መለያየት ምክንያት የምወዳትን ባለቤቴንና ልጆቼን እንዳላጣቸው እፈራለሁ''

***ክፍል አንድ***

ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች እንደምን ሰነበታችሁ ስሜ ጸጋ ሥላሴ ይባላል የምኖረው ወሊሶ ከተማ ሲሆን በየጊዜው የሚወጡ ጽሑፎቻችሁን አነባለሁ። እናም እኔም በትዳር ሕይወቴ ችግር የሆነብኝን ጉዳይ እንደሚከተለው ጻፍኩላችሁ። እኔና ባለቤቴ ትውውቃችን ዩኒቨርስቲ እያለን ነበር አሁን የአንድ ወንድ ልጅና የአንዲት ሴት ልጅ ወላጆች ሆነናል። ከተጋባን ድፍን ፲፪ ዓመት ሞላን። ነገር ግን በወቅቱ እኔም የነበረኝ የእምነት ጥንካሬ የላላ በመሆኑ የትዳሬ ዋና ጉዳይ እምነት መሆኑን ብዙም አስተውዬ አላውቅም ነበር። እናም ትዳራችንን በመግባባትና በመፈቃቀድ ላይ አድርገን መሠረትን። እየቆየን በዕድሜም ሆነ በአእምሮ እየጎለመስን ስንመጣ ባለቤቴ የቤተሰቤ እምነት የምትለውን እስልምና አጥብቃ በመከታተል በኔና በልጆቼ ላይም ተጽዕኖ ማድረግ ጀመረች። ልጆቼን ባላት ትርፍ ጊዜ የእስልምና ትምህርት ማስተማር፣ ወደ ቁርአን ቤት መላክ ወዘተ የመሳሰሉትን ነገሮች ማከናወን ጀመረች። ከዚያ ጊዜ ወዲህ ተነጋግረን መግባባትና መፍትሔ ማምጣት አልቻልንም። ስለዚህ እኔ ብዙ ዓለማዊ የመፍትሔ አማራጮችን ተጠቅሜ ትዳሬንና ልጆቼን ለማቆየት ሞክሬ ነበር። አሁን ግን ሁሉም ነገር ቁልቁል ሆነብኝ እናም በእናንተ በኩል መንፈሳዊ ምክርና አስተማሪ መፍትሔ እንዲሰጠኝ እፈልጋለሁ። ከልጆቼም ከባለቤቴም ተለይቼ ባልኖር ግን እመርጣለሁ። ምክንያቱም ብቸኝነት ያስፈራኛል።

የተከበርክ ውድ ወንድማችን በቅድሚያ በገጠመህ ችግር ብቻህን ከመጨነቅ ይልቅ መፍትሔ አገኛለሁ ብለህ ያስጨነቀህን ጉዳይ ስላካፈልከን እናመሰግንሃለን። እኛም በዝርዝር ያነሳኸውን ታሪክ መነሻ በማድረግ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ መሠረት በማድረግ ለገጠመህ ችግር መፍትሔ ይሆናሉ ብለን ያሰብናቸውን ምላሾች ከዚህ በታች ይዘን ቀርበናል፤ መልካም ንባብ።

ውድ ጠያቂያችን አብዛኛውን ጊዜ ትዳር አደጋ ውስጥ የሚገባው ወይም ባልና ሚስት የሚፋቱትና ልጆች የሚበተኑት ቅድመ ጋብቻ ላይ በሚፈጸም የጥንቃቄ ጉድለትና ትክክል ያልሆነ የትዳር አመሠራረት ሂደት ነው። የቅድመ ጋብቻ የትውውቅ ወቅት ወይም የትውውቅ ጊዜ የጥንዶቹ የትዳር ሕይወት መሠረት የሚጣልበት ወርቃማ ጊዜ ነው። በዚህ ወቅት በስሜታዊነት፣ በችኮላ ወይም በግዴለሽነት በሚደረግ ውሳኔ የሚፈጠሩ ስሕተቶች በስተኋላ ያልተጠበቀ ዋጋ ማስከፈላቸው አይቀርም።

ትዳር ተቃራኒ ጾታ ባላቸው ጥንዶች የሚመሠረት፣ ለትልቋ ቤተ ክርስቲያን ሁለንተናዊ አገልግሎት ስኬታማነት መሠረት የሆነ ቤተሰብን ያቀፈ የተቀደሰ አንድነት ነው። በምድራዊ መንግሥት አንጻር ካየንም ትዳር ትንሹ መንግሥት በመሆን ለትልቁ መንግሥት ግንባታ በመሠረትነት ያገለግላል። ትንሿ ቤተ ክርስቲያንና ትንሹ መንግሥት የሚጀምረው በተቀደሰ ጋብቻ ከሚመሠረት ትዳርና ቤተሰብ ነው የሚባለው ለዚህ ነው። ትዳር ለአመሠራረቱ፣ ለውጤታማነቱና ለዘላቂነቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግለት የሚገባ ልዩ ተቋም ነው።

ውድ ጠያቂያችን ስለትዳርህ እንደገለጽከው ከሆነ ቀድሞ መሠራት የሚገባውን ቅድመ ዝግጅት ባግባቡ መሥራት ባለመቻልህ የትዳራችሁ መሠረት በመናጋት ላይ መሆኑን ተረድተናል። ብዙ ጊዜ

የውበትን ትክክለኛ ትርጉም ስለምናዛባው በራሳችን የእይታ ስሕተት በወጥመድ ተይዘን እንሠቃያለን፡፡ የአንድ ሰው ትክክለኛ ውበት አፍኣዊና ውሳጣዊ በሚሉ ሁለት ክፍሎች ተከፍሎ ይገለጻል፡፡ በሌላም መልኩ የሰው ማንነት ሲጠና በተመሳሳይ ሁኔታ ውጪያዊና ውስጣዊ ማንነት ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ አፍኣዊ (ውጪያዊ) ውበት (ማንነት) መገለጫው ውጪያዊ ገጽታ ነው፡፡ ይህም ተክለ ሰውነትን፣ አኗኗርን፣ አለባበስን፣ አነጋገርን፣ ጠባይን፣ ሥራውንና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡ ውሳጣዊ ውበት (ማንነት) ደግሞ ባሕርይውን፣ ፍልስፍናውን ማለትም የሕይወት እይታውን፣ ዕውቀቱን፣ አስተሳሰቡን፣ እምነቱን፣ ምኞቱን፣ ስሜቱንና ማኅበራዊ ዕሴቱን ያጠቃልላል፡፡

> **ክርስቲያን በእምነት የማትመስለውን ሚስቱን ይቀድሳል የሚለው ኀይለ ቃል የሚያሳየው አማኙ ባል የማታምን ሚስቱን የሚቀድስበት ኀይል እንዳለው ነው፡፡**

በአግባቡ ካልተያዘ መረጋጋትንና ማስተዋልን በሚጋርደው የወጣትነት ዕድሜ ጎልቶ የሚታየው ውጪያዊ ውበትና ማንነት ይሆንና ተፈጥሮአዊ በሆነው አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ለውጥ እየታገዘ በስሜት ማዕበል ይናወጻል፡፡ አፍኣዊው ገጽታ ውሳጣዊውን ውበት እንዳናይ አሳውሮ በጭፍን የመንዳት አቅም እንዲያገኝ ዕድል ከሰጠነው ወደማንወጣበት ዐዘቅት ይከተናል፡፡ ብዙዎች እኅቶቻችንና ወንድሞቻችንን አታሎ ገደል የሚከታቸው ደግሞ ውስጣዊው ማንነት በውጪያዊው ማንነት በሚደበቅበት ጊዜ ነው፡፡ ውስጣዊው ማንነት በውጪያዊው ማንነት ካባ በሚሸፈንበት ጊዜ እጅግ አደገኛ ይኾናል፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጊዜ የአንድን ሰው ትክክለኛ ማንነት መረዳት አስቸጋሪ ስለሚኾን ነው፡፡ አንድ ሰው ውሳጣዊ ማንነቱ በተለይም መንፈሳዊ ሕይወቱ የላላ ከኾነ በሌሎች ውጪያዊ ውበት በቀላሉ የሚማረክ መኾኑ አይቀሬ ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ችግር ብዙ ወጣቶችን አታሎ ወደማይጠቅም ሕይወት ውስጥ አስገብቷቸዋል፡፡ ወንድማችን አንተም የችግርህ ምንጭ ከእነዚህ ነጥቦች ውጪ ሊሆን እንደማይችል ከጻፍከልን ጥያቄ መረዳት እንችላለን፡፡

ውድ ጠያቂያችን ምንም እንኳን መፍትሔ የሚሰጠው እግዚአብሔር ቢሆንም በማኅበረሰቡ ውስጥ ስንኖር ለችግሮቻችን መፍትሔ ሰጪ የሚሆኑ ሰዎችና ተቋማት በመኖራቸው እንደ እግዚአብሔር በሰው ላይ አድሮ ችግርን ይፈታልና እኛም ካህናትንና ሊቃውንት አባቶችን በማማከር ያገኘነውን ምክረ ሀሳብና ሃይማኖታዊ መፍትሔዎች ብሎም በኦርቶዶክሳዊ ሕይወትህ ልትጠቀምባቸው ይገባሉ ያልናቸውን መፍትሔዎች እንደሚከተለው አስቀምጠናል፡፡

### ፩. አሁን ያላችሁበትን የትዳር ሁኔታ በጥልቀት መመርመር

ውድ ጠያቂያችን እንደገለጽከው ደግሞ በ፲፪ ዓመት የትዳር ቆይታችሁ ፪ ልጆችን እስከ ማፍራት ደርሳችኋል፡፡ ባለቤትህ በስተኋላ ባንተና በልጆቻችሁ ላይ እያደረሰች ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ገልጸህ “እንዴት ነው መቋቋምና ማስተካከል የምችለው?” ብለህ ጠይቀኸናል፡፡ ይህ የአንተ ዓይነት ችግር በመጽሐፍ ቅዱስም ተመዝገቦ የሚገኝ የነበረ፣ ያለና የሚኖር የብዙዎች ምእመናን ፈተና ነው፡፡ ለምሳሌ በመጽሐፈ

ዕዝራ እንዲህ የሚል ሃሳብ እናገኛለን"ካህኑም ዕዝራ ተነሥቶ፥ ተላልፋችኋል፤ የእስራኤልን በደል ታበዙ ዘንድ እንግዶችን ሴቶች አግብታችኋል። አሁንም የአባቶቻችንን አምላክ እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ደስ የሚያሰኘውንም አድርጉ፤ ከምድርም አሕዛብና ከእንግዶች ሴቶች ተለዩ፤ አላቸው።" (ዕዝ. ፲፥፲-፲፪) የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጥሰው ከእንግዶች ሴቶች ጋር የተጋቡ በርካታ ወንዶች መገኘታቸውን ካህኑ ዕዝራ በስም በስማቸው ዘርዝሮ፦ "እነዚህ ሁሉ እንግዶቹን ሚስቶች አግብተው ነበር፤ ከእነዚህም ሚስቶች ዐያሌዎቹ ልጆችን ወልደው ነበር።" (ዕዝ. ፲፥፵፬) ይላል።

ቅዱስ መጽሐፋችን ባልና ሚስት አንድ አካል መሆናቸውን ያስተምረናል። አንድ አካል መሆን እውን የሚሆነው ደግሞ ጥንዶቹ በሁሉም ነገር ፍጹም የሆነ ተዋሕዶ ሲኖራቸው ነው። "ከወንድሞቻችን መካከል የማታምን፥ ባልዋንም የምታፈቅር ከእርሱም ጋር ለመኖር የምትወድ ሚስት ያለችው ሰው ቢኖር ሚስቱን አይፍታ። ሴቲቱም የማያምንና ሚስቱን የሚያፈቅር ከእርስዋም ጋር ሊኖር የሚወድ ባል ቢኖራት ባልዋን አትፍታ። የማያምን ባል በሚስቱ ይቀደሳልና፤ የማታምን ሚስትም በባልዋ ትቀደሳለችና፤ ያለዚያማ ልጆቻችው ርኩሳን ይሆናሉ፤ አሁን ግን ቅዱሳን ናቸው።. . . ሚስትም ባልዋን ታድነው እንደ ሆነ አታውቅምና፤ ባልም ሚስቱን ያድናት እንደ ሆነ አያውቅምና።" (፩ ቆሮ. ፯፥፲፪-፲፯) በቅድሚያ የምናነሣው ነጥብ የማታምን ሚስትን ፥ ወይም የማያምን ባልን መፍታት አይገባም የሚለው ነው። መረሳት የሌለበት ጉዳይ ሐዋርያው ኢአማኒ የትዳር አጋርን አትፍቱ ሲል ያስቀመጣቸውን መሠረታዊ መሥፈርቶች የሚያሟላ/የምታሟላ ከሆነ/ች ነው። እነዚህም የማታምን ሚስት ባልዋን የምታፈቅርና ከእርሱ ጋር ለመኖር የምትወድ ከኾነች የሚለው ነው። የማያምን ባልም በተመሳሳይ ሚስቱን የሚያፈቅርና ከእርስዋ ጋር ሊኖር የሚወድ ከሆነ ከሆነች አይፍታት፤ አትፍታው ብሏል። እዚህ ላይ በጥንቃቄ መታየት ያለበት አንዱ ጉዳይ ሐዋርያው በመልእክቱ የሚያምን ክርስቲያን እምነቱ የማትመስለውን እንዲያገባ ፈቃድ እየሰጠ ነው ማለት አይደለም። የማያምን ባል ስላላት ሚስት ወይም የማታምን ሚስት ስላለችው ባል ነው እየተናገረ ያለው እንጂ ወደፊት በዚህ መስመር ስለሚጋቡት አለመሆኑን ልብ ማለት ይገባል። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ተመሥርቶ ችግር ውስጥ ስላሉት ነው እያስተማረ ያለው።

ውድ ወንድማችን አንዱ መመርመር ያለብህ ነጥብ ይህ ነው። ሚስትህ እነዚህን ነጥቦች የምታሟላ ካልሆነ አብራ ልትኖር የምትችልባቸውን ዕድሎች ልታጣ ትችላለች። የዚህም ምክንያቱ ራሷ ነች። ዳሩ ግን መሥፈርቶቹን የምታሟላ ከሆነች አንተም በተመሳሳይ የምታፈቅራትና አብረሃት ለመኖር የምትፈልግ ከሆነ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን ልትፈታ አይገባትም። እንዳየነውም ሐዋርያው አብሮ የመኖርንና ያለመኖርን መብትና ነፃነት በባልና በሚስት ፍላጎትና ውሳኔ ላይ ነው ያኖረው። ሐዋርያው ለምንድነው አማኙ ባል ከማታምነው ሚስቱ ጋር እንዲኖር የፈቀደው? ለሚለው ጥያቄም፦ "የማታምን ሚስት በባሏ ትቀደሳለች፤. . .ባልም ሚስቱን ያድናት እንደኾነ አያውቅምና።" በማለት ተገቢውን ምላሽ ሰጥቷል።

ክርስቲያን በእምነት የማትመስለውን ሚስቱን ይቀድሳል የሚለው ኀይለ ቃል የሚያሳየው አማኙ ባል የማታምን ሚስቱን የሚቀድስበት ኀይል እንዳለው ነው። ምንድን ነው ያ ኀይል? የክርስትና ሃይማኖት ፍጹም እምነት በመሆኑ የዚህ እምነት ባለቤት (ክርስቲያን) እንደተገለጸው በኢአማኒው እምነት እስካልተጠለፈ ድረስ በማንኛውም ዓይነት እምነት መሰል አስተሳሰብ አይረክስም። በተቃራኒው ይህ እውነተኛውን የባሕርይ አምላክ (እግዚአብሔርን) የሚያመልክና ሀብተ ወልድና ተቀብሎ በስሙ የተጠራ ክርስቲያን ማንኛውንም ዓይነት ከክርስትና የተለየ አማኝን ይቀድሳል።

*ይቀጥላል...*